https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ማውጫ

የዕውቀትና የሥልጣኔ መንገድ
እስላምና ዕውቀት
የስልጣኔ መንገድ ፦
የስልጣኔ መንገድ መደላደሎች
.የቁርኣንና የሱንና ታአምራት

የዕውቀትና የሥልጣኔ መንገድ

https://www.path-2-happiness.com/am

የዕውቀትና የሥልጣኔ መንገድ

እስላምና ዕውቀት

https://www.path-2-happiness.com/am

የደስተኝነት መንገድ በምንም ዓይነት በማይምነትና ኋላ ቀርነት ሸለቆ ውስጥ ሊያልፍ ስለማይችል፣የግድ የዕውቀትና የሥልጣኔን ጎዳና አቋርጦ ሚያልፍ መሆኑ ጥርጥር ለውም። እንደ እስላም ሃይማኖት የዕውቀትና የዐዋቂዎችን ደረጃ ከፍ ያደረገ፣ለዐዋቂዎችና ለምሁራን ክብር አያያዝ የደነገገ፣የትምህርትና የዕውቀት ግብይትን ያበረታታ፤ አእምሮን ለመጠቀም፣ለማስተዋልና ለማስተንተን ጥሪ ያደረገ አንድም ሌላ ሃይማኖትም ሆነ ርእዮተ ዓለም የለም። ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ ያስተማሩትና ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ በዓለም ማእዘናት የተሰራጨን ታላቅ ሥልጣኔ እንዳስገኘው የእስላም ሃይማኖት፣ለዕውቀት ታላቅ ትኩረት የሰጠ ሌላ እምነትም ሆነ አመለካከት ከቶም አልተገኘም። ስለዚህም ለእውቀትና ለመንፈሱ እንግዳ በሆነ አካባቢ ውስጥ የነቢዩ ﷺ መላክ፣እውነተኛው የዕውቀት አብዮት ተደርጎ የሚቆጠር ነው። እስላም የመጣው የዕውቀትን ጮራ ለማፈንጠቅና ምድረ ዓለሙን በመለኮታዊ መመሪያ ብርሃኑ ለማዳረስ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَفَحُكۡمَ ٱلۡجَٰهِلِيَّةِ يَبۡغُونَۚ وَمَنۡ أَحۡسَنُ مِنَ ٱللَّهِ حُكۡمٗا لِّقَوۡمٖ يُوقِنُونَ ۝٥٠} [المائدة: ٥٠]،

‹‹የማይምነትን ፍርድ ይፈልጋሉን? ለሚያረጋግጡም ሕዝቦች ከአላህ ይበልጥ ፍርዱ ያማረ ማን ነው?››[አል ማእዳህ:50]

በዚህ ሃይማኖት ውስጥ ለማይምነት፣ለባዶ ግምትም ሆነ ለጥርጣሬ ቦታ የለም። ወደማያነበውና ወደማይጽፈው ነቢይ ﷺ በመጀመሪያ ከአላህ (ሱ.ወ.) የተላለፈው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለው ነበር፦

{ٱقۡرَأۡ بِٱسۡمِ رَبِّكَ ٱلَّذِي خَلَقَ ۝١ خَلَقَ ٱلۡإِنسَٰنَ مِنۡ عَلَقٍ ۝٢ ٱقۡرَأۡ وَرَبُّكَ ٱلۡأَكۡرَمُ ۝٣ ٱلَّذِي عَلَّمَ بِٱلۡقَلَمِ ۝٤ عَلَّمَ ٱلۡإِنسَٰنَ مَا لَمۡ يَعۡلَمۡ ۝٥} [العلق: ١ - ٥]،

‹‹አንብብ፣በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም። ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)። አንብብ፤ጌታህ በጣም ቸር ሲኾን፤ያ በብርዕ ያስተማረ፤ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲኾን።››[አል ዐለቅ:1-5]

ይህ የመጀመሪያው ርእሰ ጉዳይ ይህን ሃይማኖት ለመረዳት የመክፈቻ ቁልፍ ነው፤የዚችን ዱንያ ሕይወት ብቻ ሳይሆን የሰው ልጆች ሁሉ መመለሻ የሆነውን የወዲያኛውን የአኼራ ሕይወት ለማወቅም የመክፈቻ ቁልፍ መሆኑ ግልጽ ነው።

ቁርኣን ለዓለም ጉዳዮች ትኩረት የሰጠው የሰጠው ገና መተላለፍ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ መሆኑን ማስተዋል ይቻላል። እንዲያውም ቅዱስ ቁርኣን በአንቀጾቹ ውስጥ እንደ ተረከው ሁሉ ገና የሰው ልጅ ፍጥረት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነው ማለት ይቻላል። አላህ (ሱ.ወ.) ኣደምን ፈጥሮ በምድር ላይ ተጠሪ ምትክ አድርጎታል፤መላእክት ይሰግዱለት ዘንድም አዟል፤አክብሮታል፤ደረጃውን ከፍ አድርጎ አልቀቀታልም። የዚህ ከበሬታና ልቅና ምክንያት ምን እንደሆነ ለኛና ለማእክቱም ግልጽ አድርጎ መንስኤው ‹‹ዕውቀት›› መሆኑን አሳውቋል። ይህንኑ በማረጋገጥ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذۡ قَالَ رَبُّكَ لِلۡمَلَٰٓئِكَةِ إِنِّي جَاعِلٞ فِي ٱلۡأَرۡضِ خَلِيفَةٗۖ قَالُوٓاْ أَتَجۡعَلُ فِيهَا مَن يُفۡسِدُ فِيهَا وَيَسۡفِكُ ٱلدِّمَآءَ وَنَحۡنُ نُسَبِّحُ بِحَمۡدِكَ وَنُقَدِّسُ لَكَۖ قَالَ إِنِّيٓ أَعۡلَمُ مَا لَا تَعۡلَمُونَ ۝٣٠ وَعَلَّمَ ءَادَمَ ٱلۡأَسۡمَآءَ كُلَّهَا ثُمَّ عَرَضَهُمۡ عَلَى ٱلۡمَلَٰٓئِكَةِ فَقَالَ أَنۢبِـُٔونِي بِأَسۡمَآءِ هَٰٓؤُلَآءِ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ۝٣١ قَالُواْ سُبۡحَٰنَكَ لَا عِلۡمَ لَنَآ إِلَّا مَا عَلَّمۡتَنَآۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلۡعَلِيمُ ٱلۡحَكِيمُ ۝٣٢ قَالَ يَٰٓـَٔادَمُ أَنۢبِئۡهُم بِأَسۡمَآئِهِمۡۖ فَلَمَّآ أَنۢبَأَهُم بِأَسۡمَآئِهِمۡ قَالَ أَلَمۡ أَقُل لَّكُمۡ إِنِّيٓ أَعۡلَمُ غَيۡبَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَأَعۡلَمُ مَا تُبۡدُونَ وَمَا كُنتُمۡ تَكۡتُمُونَ ۝٣٣} [البقرة: ٣٠ - ٣٣].

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ ለመላእክት ፦ እኔ በምድር ላይ ምትክን አድራጊ ነኝ፤ባለ ጊዜ፣(የኾነውን አስታውስ፤እነርሱም) እኛ ከማመስገን ጋር የምናጠራህ፣ላንተም የምንቀድስ ስንኾን በርሷ ውስጥ የሚያጠፋንና ደሞችንም የሚያፈስን ታደርጋለህን? አሉ፤(አላህ) እኔ የማታውቁትን ነገር ዐውቃለሁ አላቸው። አደምንም ስሞችን ሁሏንም አስተማረው፤ከዚያም በመላእክት ላይ (ተጠሪዎቹን) አቀረባቸው፤እውነተኞችም እንደ ኾናችሁ የነዚህን (ተጠሪዎች) ስሞች ንገሩኝ፣አላቸው። ጥራት ይገባህ፤ከአስተማርከን ነገር በስተቀር ለኛ ዕውቀት የለንም፤አንተ ዐዋቂው ጥበበኛው አንተ ብቻ ነህና (አሉ)። ፦ አደም ሆይ! ስሞቻቸውን ንገራቸው አለው፤ስሞቻቸውን በነገራቸውም ጊዜ፣እኔ የሰማያትንና የምድርን ሩቅ ምስጢር ዐውቃለሁ፤የምትገልጹትንና ያንንም ትደብቁት የነበራችሁትን ዐውቃለሁ አላልኳችሁምን? አላቸው።››[አል በቀራህ: 30-33]

ዕውቀት እስላም ውስጥ ያለውን አስፈላጊነትና የላቀ ደረጃ የተሰጠው መሆኑን ከሚያመለክቱ ነገሮች አንዱ፣ስለ ዕውቀት የተነገረው በፍጥረት ጅማሮ ላይ ብቻ አለመሆኑ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

https://www.path-2-happiness.com/am

‹‹ብብንአ›› {ٱقۡرَأۡ}

ይህ አካሄድ በዘላለማዊው ሕያው መጽሐፍ ውስጥ፣በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ ተዘዋዋሪ መንገድ ስለ ዕውቀት ሳያነሳ የሚያልፍ አንድም ሱራ (ምዕራፍ) የለም ማለት በሚያስችል ሁኔታ የጸና አካሄድ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) ከሁሉም በላይ ታላቅ በሆነው የተውሒድ ትእይንት ላይ እንኳ ለዕውቀት ጥሪ አድርጎ ለግብይቱ ትእዛዝ አስተላልፏል። ይህን በተመለከተም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَٱعۡلَمۡ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا ٱللَّهُ وَٱسۡتَغۡفِرۡ لِذَنۢبِكَ وَلِلۡمُؤۡمِنِينَ وَٱلۡمُؤۡمِنَٰتِۗ وَٱللَّهُ يَعۡلَمُ مُتَقَلَّبَكُمۡ وَمَثۡوَىٰكُمۡ ۝١٩} [محمد: ١٩]؛

‹‹እነሆ ከአላህ ሌላ አምላክ አለመኖሩንም እወቅ፤ስለ ስሕተትህም፣ለምእመናንም ምሕረትን ለምን፤አላህም መዘዋወሪያችሁን፣መርጊያችሁንም ያውቃል።››[ሙሐመድ፡19]

የዕውቀትና የዐዋቂዎችን ብልጫና ደረጃ ማመልከት ብቻ ሳይሆን ዐዋቂዎችና ማይማን እኩል አለመሆናቸውንም አረጋግጧል፦

{قُلۡ هَلۡ يَسۡتَوِي ٱلَّذِينَ يَعۡلَمُونَ وَٱلَّذِينَ لَا يَعۡلَمُونَۗ إِنَّمَا يَتَذَكَّرُ أُوْلُواْ ٱلۡأَلۡبَٰبِ ۝٩} [الزمر: ٩]،

‹‹እነዚያ የሚያውቁና እነዚያ የማያውቁ፣ይተካከላሉን? በላቸው የሚገነዘቡት ባለ አእምሮዎቹ ብቻ ናቸው።››[አል ዙመር፡9]

ዕውቀት የተሰጡ ሰዎች በወዲያኛው የኣኼራ ሕይወት ከሚያገኙት ታላቅ ምንዳ ባሻገር፣በዚህ ዓለም ላይም የላቀ ደረጃና ማእረግ ተሰጥቷቸዋል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَرۡفَعِ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مِنكُمۡ وَٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡعِلۡمَ دَرَجَٰتٖۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ خَبِيرٞ ۝١١} [المجادلة: ١١]،

‹‹አላህ ከናንተ እነዚያን ያመኑትንና እነዚያንም ዕውቀትን የተሰጡትን በደረጃዎች ከፍ ያደርጋል፤አላህም በምትሠሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው።››[አል ሙጃደለህ፡11]

ከዚህም ሌላ ቅዱስ ቁርኣን ውስጥ ከዕውቀት በስተቀር ጭማሬ እንዲጠየቅበት

አንብብ . . የእስላም ጥሪ

‹‹እስላም - የሳይንስና የዕውቀት ሃይማኖት ነውና - ዕውቀት እንዲገበዩና የተማሩትንም ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለተከታዮቹ ጥሪ የሚያደርግ መሆኑ ጥርጥር የለውም። የቅዱስ ቁርኣን የመጀመሪያው አንቀጽ ‹‹አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም።›› የሚለው የአላህ (ሱ.ወ.) ቃል በመሆኑ ይህን ማድረጉም አስገራሚ አይደለም።››

ሮበርት ቢየር ጆዜፍ
በፈረንሳይ ዩኒቨርሲቲዎች የፍልስፍና ፕሮፌሰር

የተበረታታ ሌላ ምንም ነገር አልተጠቀሰም። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَقُل رَّبِّ زِدۡنِي عِلۡمٗا ۝١١٤} [طه: ١١٤]؛

‹‹ጌታዬ ሆይ! ዕውቀትንም ጨምርልኝ በል።››[ጣሃ፡11]

ከዚህ ስንነሳም ነቢዩ ﷺ የሚከተለውን ማለታቸው የተጋነነ አልነበረም፦ ‹‹ዕውቀት ለመገብየት ሲል መንገድ የገባውን ሰው አላህ ወደ ጀነት የሚወስደውን መንገድ ገር ያደርግለታል። መላእክትም ለተማሪው ውዴታ ክንፎቻቸውን ይዘረጋሉ፤ለዕውቀት ፈላጊ ሰው ውሃ ውስጥ የሚገኙ ዓሳዎች እንኳ ሳይቀሩ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ ምሕረት ይለምኑለታል። ዕውቀት ፈላጊው ተማሪ በአምልኮተ አላህ (ዕባዳ) ላይ በተሰማራው ሰው ላይ ያለው ብልጫ፣ጨረቃ

መስጊድ . . ዩኒቨርሲቲ ነው

‹‹መስጊዶች የእስላም ዩኒቨርሲቲዎች ነበሩ - አንዳንዶቹ ዛሬም ድረስ ናቸው። ዕውቀትን በተጠሙ ተማሪዎች የተጨናነቁ ነበሩ። እነዚህ ተማሪዎች፣ሊቃውንት በሃይማኖት፣በሕግ፣በፍልስፍና፣በሕክምና እና በሒሳብ ሳይንሶች ላይ የሚሰጡትን ሌክቸሮች ለማዳመጥ ይመጡ ነበር። ሊቃውንቶቹ ራሳቸው ዐረብኛ ይናገሩ ከነበሩ ከሁሉም የዓለም ክፍሎች የሚመጡ ነበሩ። ተማሪው ዜግነቱ የፈለገውን ቢሆን ሙሉ አቀባበል ይደረግለት ነበር።››

እስታንሊ ሊይን ፓውል
እንግሊዛዊ ሳይንቲስት

በሌሎች ከዋክብት ላይ ያለው ብልጫ ዓይነት ነው። ዑለማእ (ሊቃውንት) የነቢያት ወራሾች ናቸው፤ነቢያት ዲናርም ሆነ ድርሀም አላወረሱም፣ያወረሱት ዕውቀትን (ዕልም) ብቻ ነው፤እሱን የያዘ ሰው የበዛ የድርሻ ዕድል ወስዷል።›› [በሙስሊም የተዘገበ] ለዚህም ነው ከነቢዩ ﷺ መላክ በኋላ መስጊዶች የዕውቀት ምንጭና የሊቃውንት አምባ የሆኑት።‹‹ዕውቀት›› (ዕልም) የሚለው ቃልና የተለያዩ እርባታዎቹ በአላህ (ሱ.ወ.) መጽሐፍ ውስጥ የተደጋገመበትን ጊዜ ስንቆጥር እጅግ አስገራሚና አስደናቂ የሆነ ውጤት እናገኛለን። ቃሉ 779 ጊዜ የተደጋገመ ሲሆን፣ይህም በአማካይ በያንዳንዱ የቁርኣን ሱራ ውስጥ ሰባት ጊዜ ያህል ማለት ነው! ይህ ‹‹ዐለመ›› ከሚለው ባለ ሦስት ሆሄ ስርወ ቃሉ ብቻ ሲሆን፣የዕውቀትን ፍችና ትርጉም የያዙ ሌሎች በርካታ ቃላት ይገኛሉ። ለአብነት ያህል፦ እርግጠኝነት (የቂን)፣መመራት (አልሁዳ)፣አእምሮ (አልዐቅል)፣እሳቤ (ፍክር)፣አስተውሎ (አንነዘር)፣ጥበብ (አልሕክማ)፣ግንዛቤ (ፍቅህ)፣ብርሃን (ቡርሃን)፣ማስረጃ (ደሊል)፣አስረጅ (አልሑጅጃ)፣አንቀጽ (ኣየህ)፣ማረጋገጫ (አልበይነህ) እና ሌሎች በዕውቀት ትርጉም ስር የሚካተቱ ቃላት ይገኛሉ። የነቢዩን ሱንና በተመለከተ ከድግግሞሹ ብዛት ቁጥሩን ማወቅ አስቸጋሪ ይሆናል።

ቁርኣን የፊዚክስ፣የኬሚስትሪ፣የስነሕይወት ወይም የማቴማቲክስ መጽሐፍ ሳይሆን የሕይወት መመሪያ (የህዳያ) መጽሐፍ ነው። ይህም ሆኖ ግን በውስጡ ከተካተተው መካከል ዘመናዊ ሳይንስ ያረጋገጠውን የጸና እውነታ የሚጻረር አንድም ነገር ፈጽሞ የለበትም።

‹‹ዕውቀት›› (ዕልም) የሚለው ቃልና የተለያዩ እርባታዎቹ በአላህ (ሱ.ወ.) መጽሐፍ ውስጥ የተደጋገመበትን ጊዜ ስንቆጥር እጅግ አስገራሚና አስደናቂ የሆነ ውጤት እናገኛለን። ቃሉ 779 ጊዜ የተደጋገመ ሲሆን፣ይህም በአማካይ በያንዳንዱ የቁርኣን ሱራ ውስጥ ሰባት ጊዜ ያህል ማለት ነው! ይህ ‹‹ዐለመ›› ከሚለው ባለ ሦስት ሆሄ ስርወ ቃሉ ብቻ ሲሆን፣የዕውቀትን ፍችና ትርጉም የያዙ ሌሎች በርካታ ቃላት ይገኛሉ። ለአብነት ያህል፦ እርግጠኝነት (የቂን)፣መመራት (አልሁዳ)፣አእምሮ (አልዐቅል)፣እሳቤ (ፍክር)፣አስተውሎ (አንነዘር)፣ጥበብ (አልሕክማ)፣ግንዛቤ (ፍቅህ)፣ብርሃን (ቡርሃን)፣ማስረጃ (ደሊል)፣አስረጅ (አልሑጅጃ)፣አንቀጽ (ኣየህ)፣ማረጋገጫ (አልበይነህ) እና ሌሎች በዕውቀት ትርጉም ስር የሚካተቱ ቃላት ይገኛሉ። የነቢዩን ሱንና በተመለከተ ከድግግሞሹ ብዛት ቁጥሩን ማወቅ አስቸጋሪ ይሆናል። ቁርኣን የፊዚክስ፣የኬሚስትሪ፣የስነሕይወት ወይም የማቴማቲክስ መጽሐፍ ሳይሆን የሕይወት መመሪያ (የህዳያ) መጽሐፍ ነው። ይህም ሆኖ ግን በውስጡ ከተካተተው መካከል ዘመናዊ ሳይንስ ያረጋገጠውን የጸና እውነታ የሚጻረር አንድም ነገር ፈጽሞ የለበትም።

ይህ ሁሉ ኋላ ላይ በእስላማዊው መንግስት ላይ፣ በሁሉም የሳይንስና የዕውቀት ዘርፎች ሰፊ እንቅስቃሴ ያመጣ ጥልቅ አሻራ ነበረው። ያስገኘው ታላቅ ንቅናቄ በታሪክ ውስጥ አቻ ያልተገኘለት፣በሙስሊም ሊቃውንት አማካይነት ታላቅ ሳይንሳዊ ዕድገትና ስልጣኔን ያስመዘገበ፣ለመላው የሰው ዘር ባለውለታነቱን እንደያዘ የዘለቀ ድንቅ ሳይንሳዊ ቅርስ ለዓለም ያበረከተ ታላቅ ንቅናቄ ነበር። ማክስ ማይርሆፍ እንደሚለው ፦ ‹‹በአውሮፓ የታየው የኬሚስትሪ ዕድገት በቀጥታ የጃቢር ብን ሐያን ትሩፋት ነው ማለት ይቻላል። ለዚህ ትልቁ ማስረጃ



ቁርኣንና ሳይንሳዊ ታምራቱነው

‹‹ቅዱስ ቁርኣን ከተፈጥሮ ሳይንስ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ግልጽ አንቀጾችን አካትቷል። ፕሮፌሰር ዩሱፍ መርዋ ‹የተፈጥሮ ሳይንሶች በቅዱስ ቁርኣን› በተሰኘ መጽሐፍ ውስጥ አንቀጾቹን ያቀረቡ ሲሆን ቁጥራቸውም በትክክል 774 ነው። ዝርዝራቸውም የሚከተለው ነው፡- ማቴማቲክስ 61፣ፊዚክስ 264፣አቶሚክስ 5፣ኬሚስትሪ 29፣ሬላቲቪቲ 62፣ስነፈለክ 100፣ከባቢያዊ አየር 20፣ውሃ ነክ 14፣የጠፈር ሳይንስ 11፣ዙኦሎጂ12፣የአዝዕርት ሳይንስ 21፣ስነሕይወት 36፣ጠቅላላ ጆዖግራፊ 73፣አንትሮፖሎጂ 10፣የከርሰ ምድር ሳይንስ 20፣የዩኒቨርስና ዥነቶች ሳይንስ 36።››

ሞሪስ ቡካይፓውል

ፈረንሳዊ ሳይንቲስትና ሐኪም

እርሱ ያስገኛቸው ቴክኒካዊ የስያሜ ቃላት በተለያዩ የአውሮፓ ቋንቋዎች ውስጥ ዛሬም ድረስ በማገልገል ላይ የሚገኙ መሆናቸው ነው።››

አልዶ ሚይሊ በበኩሉ እንዲህ ይላል ፦ ‹‹ወደ ማቴማቲክስና ወደ ስነፈለክ ስንሸጋገር ደግሞ ከመጀመሪያው አንስቶ የመጨረሻውን ከፍተኛ ደረጃ የተቆናጠጡ ሊቃውንትን እናገኛለን። ከነዚህ ዕውቅ ሳይንቲስቶች መካከል አቡ ዐብደላህ ሙሐመድ ብን ሙሳ አልኸዋሪዝሚ[1] በታላላቅ የማቴማቲክስ ሊቃውንቶች ሰንሰለት ውስጥ የመነሻው አንጸባራቂ ዘለበት ነው . . መጽሐፎቹ በአውሮፓ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እስከ አስራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ለማስተማሪያነት ሲያገለግሉ ቆይተዋል።››

ዘግሬድ ሆንካህ ‹‹አትተስሪፍ ልመን ዐጀዘ ዐን አትተእሊፍ››[2] የተሰኘውን የዘህራዊ መጽሐፍ ቀዶ ጥገናን የሚመለከተውን ክፍል አስመልክታ እንዲህ ብላለች፦ ‹‹የዚህ መጽሐፍ ሦስተኛው ክፍል፣የአውሮፓን የቀዶ ጥገና ዕውቀት መሰረቶችን የጣለ፣ይህን የሕክምና ሳይንስ ቅርንጫፍ ወደ ላቀ ደረጃ ከፍ ያደረገ፣በዚህም ቀዶ ጥገናን በአናቶሚ

1 የአልጀብራ ሳይንስ መስራች፣የሕንዲ ቁጥር ሥርዓትን ያስተዋወቀ፣በሒሳብ፣በስነፈለክና በጂዖግራፊያ ላይ አያሌ ጥናቶችን ያቀረበ ሊቅ።

2 መጽሐፉ ሰላሳ ቅጾች ያሉት የሕክምና ሳይንስ ዐውደ ጥበብ ሲሆን፣በያዛቸው ዲያግራሞችና ስዕሎች ብዛት፣ደራሲው ዘህራዊ ለቀዶ ጥገና ይጠቀምባቸው በነበሩ መሳሪያዎች ዓይነትና ብዛት ልዩ የሆነ መጽሐፍ ነው። የክሬሞኒው ጄራር፣ቀዶ ጥገናን የሚመለከተውን የመጽሐፉን ክፍል በአስራ ሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደ ላቲን ቋንቋ ተርጉሞት በተለያዩ እትሞች ታትሟል። አንደኛው እትም በ1497 በቡንዱቅያ፣ሁለተኛው እትም በ1531 በባዘል፣ሦስተኛው እትም በ1778 በኦክስፎርድ ታትሟል። በተጨማሪም በዶክተር ሎው ክላርክ በአስራ ዘጠነኛው ምእተ ዓመት ወደ ፈረንሳይኛ ተተርጉሟል።

የዕውቀት ጥማትና የስልጣኔ ፍቅር

‹‹በስልጣኔ ታሪክ ውስጥ በመላው የሙስሊም ዓለም ከተከሰተው ድንገተኛ የዕውቀት ጥማትና የስልጣኔ ፍቅር ይበልጥ ውብና ድንቅ የሆነ ንቅናቄ ታይቶ አያውቅም። ከመሪው ኸሊፋ ጀምሮ እስከ ተራው ለፍቶ አዳሪ ድረስ እያንዳንዱን ሙስሊም የዕውቀት ጥማትና ተጉዞ የመማር ጉጉት በድንገት የተጠናወተው ይመስል ነበር። ይህም እስላም በሁሉም አቅጣጫ ካቀረበው ምርጡ ነገር ነበር። እንደ በግዳድ ወዳሉትና ከዚያም በኋላ የስነ ጽሑፍና የተለያዩ የዕውቀት ዘርፎች ማዕከሎች ወደነበሩት የትምሕርት ተቋማት የሚጎርፉት ተማሪዎች፣ዘመናዊውን ሳይንስ ለማጥናት በአውሮፓውያን ሊቃውንት ይጥለቀለቁ እንደነበሩ ዩኒቨርሲቲዎች ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ከዚያም ይበልጥ ድንቅና አስደማሚ ነበር።››

እስታንሊ ሊይን ፓውል

እንግሊዛዊ ሳይንቲስት

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ጉስታፍ ሎቦንጋውል
ፈረንሳዊ ታሪክ ጸሐፊ

የዕውቀት ስልጣኔየስልጣኔ ፍቅር

‹‹የዐረብ ስልጣኔን፣ሳይንሳዊ መጽሐፎቻቸውን፣ሳይንሳዊ ግኝቶቻቸውንና ስነ ጥበባቸውን በጥልቀት በአጠናን ቁጥር፣አዳዲስ እውነታዎችና ሰፋፊ አድማሳት ይገለጡልናል። ዐረቦች በመካከለኞቹ ክፍለ ዘመናት ለቀደምቶቹ ዕውቀቶች መታወቅ ባለውለታዎች መሆናቸውን፣የምዕራባውያን ዩኒቨርሲቲዎችም ከነርሱ ድርሰቶችና ሥራዎች ውጭ ለአምስት ምእተ ዓመታት ሌላ ምንም ምንጭ ኖሯቸው እንደማያውቅ፣አውሮፓን በቁሳዊ አእምሯዊና ስነምግባራዊ ጎኖች ያሰለጠኗት እነሱ መሆናቸውን፣በአጭር ጊዜ ውስጥ እነሱ ያመረቱትን ያህል የዕውቀትና የስልጣኔ ምርት ያመረተ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አንድም ሕዝብ አለመኖሩንና በጥበባዊና ቴክኒካዊ ፈጠራ አንድም ሕዝብ ያልበለጣቸው መሆኑንም እንገነዘባለን።››

ሳይንስ ላይ የተመረኮዘ ራሱን የቻለ መስክ እንዲሆን ያደረገ በመሆኑ፣አውሮፓ ውስጥ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል።›› ይህ የዘህራዊ መጽሐፍ ለአምስት ምእተ ዓመታት በአውሮፓ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በማስተማሪያነት ያገለገለ ከመሆኑም ባሻገር ለአውሮፓውያን የቀዶ ጥገና ሐኪሞች ዋቢና ማጣቀሻ ሆኖ የቆየ በመሆኑ በአውሮፓ ሕዳሴ ውስጥ ትልቅ ተጽእኖ ነበረው።

ሙስሊም ሊቃውንት ዛሬም ድረስ ለሰው ልጆች አበርክቶአቸውን ቀጥለዋል። አሕመድ ዙወይል(1) ‹‹የሳይንስ ዘመን›› በተባለ መጽሐፍ ውስጥ፦ ‹‹ሥራዬ ከቦታ አንጻር ቅንጣቶች በሚዋሐዱበትና በሚለያዩበት በአቶሞች እምብርት ላይ፣ከጊዜ አኳያ ደግሞ አንዲቱ ሰከንድ ግዙፍ ዘመን ወደምትሆንበት በሰከንድ ላይ ያረፈ ነው።›› ብለዋል።

እናም ሙሐመድ ﷺ ይዘውት የመጡት ይህ ዕውቀት፣ቅን መመሪያና ብርሃን፣የሰው ልጆችን ከተበከለ አረንቋ አውጥቶ ለዘመናት በዕውቀት፣በስልጣኔና በዕድገት ጎዳና ከፍ ያደረጋቸው መሆኑ በጣም ግልጽ ነው።

እስላም የሳይንሳዊ ሜቶዶሎጂን መንገድ ይዞ የመጣ ሲሆን፣ለምሳሌ ያህል እስላም ከጭፍን ተከታይነት ያስጠነቅቃል። አላህ (ሱ.ወ.) ጣዖታውያንን አስመልክቶ እንዲህ ይላል፦

{قَالُواْ بَلۡ نَتَّبِعُ مَآ أَلۡفَيۡنَا عَلَيۡهِ ءَابَآءَنَآۚ أَوَلَوۡ كَانَ ءَابَآؤُهُمۡ لَا يَعۡقِلُونَ شَيۡـٔٗا وَلَا يَهۡتَدُونَ ١٧٠} [البقرة: ١٧٠]،

1 ብርሃንን የሚተነትንና በፌምቶሰከንድ ፍጥነት የሚሠራ ካሜራ (Femtosecond Spectroscopy) በመፍጠራቸውና መሳሪያውን በመጠቀም ባደረጉት የኬሚካላዊ ንጥረነገሮች መስተጋቢር ምርምራቸው በ1999 በኬሚስትሪ የኖቤል ተሸላሚ የሆኑ ግብጻዊ የኬሚስትሪ ሊቅ ናቸው። በዚህ ጥናታቸው ዓለምን በመላ የሰው ልጅ ይደርስበታል ተብሎ ወደማይጠበቅ አዲስ የጊዜ ቀመር አስገብቷል። ይህም በኬሚካላዊ መስተጋቢሮች ሂደት ወቅት አቶሞች በቅንጣቶች ውስጥ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በፈጣን የሌዘር ቴክኖሎጂ አማካይነት መከታተል በመቻላቸው ነው። ዶክተር አሕመድ ዙወይል ሌዘርን በመጠቀም የሚሰራ፣ቅንጣቶች ሲፈጠሩና እርስ በርስ ሲዋሐዱ መከታተል የሚያስችል፣እጅግ በጣም ፈጣን የሆነ የካሜራ ሲስተም ፈልስፈዋል። ፎቶግራፉ የሚነሳበት የጊዜ አሃድ ፌምቶ ሰከንድ ሲሆን ይህም የአንድ ሰከንድ የአንድ መቶ ቢሊዮን ክፍልፋይ አንዱ ክፍል ነው።

ቁርኣን ታምራዊ ነው

‹‹ከሳይንስና ‹‹ከተፈጥሮ ጋር ትስስር ያላቸውን የቁርኣን አንቀጾች ሁሉ ተከታትያለሁ። አንቀጾቹን ከዘመናዊው ዕውቀታችን ጋር ሙሉ በሙሉ የሚጣጣሙ ሆነው አግኝቻለሁ። ሙሐመድ ﷺ ከአንድ ሺህ ዓመት ከሚበልጥ ዘመን በፊትና ከሰው ልጅ መካከል ይህን ማስተማር የሚችል አስተማሪ ከመኖሩ አስቀድሞ ጥሬውን ግልጽ እውነታ ይዞ እንደመጣም እርግጠኛ ሆኛለሁ። እኔ እንዳደረግሁት ሁሉ ቁርኣናዊ አንቀጾችን፣እያንዳንዱ የሳይንስና የጥበብ ሰው ከተሰማራበትና በሚገባ ከተማረው የሳይንስ ወይም የስነ ጥበብ የዕውቀት ዘርፍ ጋር ቢያነጻጽር፣አስተዋይና ከድብቅ ዓለማ የጸዳ እስከ ሆነ ድረስ ያለ ምንም ጥርጥር ለቁርኣን እጁን ይሰጣል።››



ሬይነህ ጂኖ
ፈረንሳዊ ፈላስፋ

‹‹አይደለም፣አባቶቻችንን በርሱ ላይ ያገኘንበትን ነገር እንከተላለን ይላሉ፣አባቶቻቸው ምንም የማያውቁና (ወደ እውነት) የማይመሩም ቢኾኑ (ይከተሉዋቸዋለን?)››[አል በቀራህ:170]

ከሳይንሳዊ ስልት ውጭ በሆነ መንገድ ግምትና ጥርጣሬ መከተልን አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِن يَتَّبِعُونَ إِلَّا ٱلظَّنَّ وَإِنۡ هُمۡ إِلَّا يَخۡرُصُونَ ١١٦} [الأنعام: ١١٦]،

‹‹ጥርጣሬን እንጅ ሌላን አይከተሉም። እነርሱም የሚዋሹ እንጂ ሌላ አይደሉም።››[አል አንዓም:116]

ዕውቀትን፣ሎጂክን፣አእምሮንና ምርምርን የሚጻረረውን ግላዊ ዝንባሌን አስመልክቶም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِنَّ كَثِيرٗا لَّيُضِلُّونَ بِأَهۡوَآئِهِم بِغَيۡرِ عِلۡمٍ} [الأنعام: ١١٩]،

‹‹ብዙዎቹም ያለ ዕውቀት በዝንባሌዎቻቸው ያሳስታሉ፤››[አል አንዓም:119]

ከፍትሕ የሚያርቀውን ጥላቻ አስመልክቶም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَا يَجۡرِمَنَّكُمۡ شَنَـَٔانُ قَوۡمٍ عَلَىٰٓ أَلَّا تَعۡدِلُواْۚ ٱعۡدِلُواْ هُوَ أَقۡرَبُ لِلتَّقۡوَىٰۖ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ خَبِيرُۢ بِمَا تَعۡمَلُونَ ٨} [المائدة: ٨]،

‹‹ሕዝቦችንም መጥላት፣ባለማስተካከል ላይ አይገፋፋችሁ፤አስተካክሉ፤እርሱ (ማስተካከል) ለአላህ ፍራቻ በጣም የቀረበ ነው። አላህንም ፍሩ። አላህ በምትሠሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው።››[አል ማእዳህ:8]

ሳይንሳዊ ነባራዊነትንና ተጨባጭነትን አስመልክቶም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{مِّنَ ٱلَّذِينَ هَادُواْ يُحَرِّفُونَ ٱلۡكَلِمَ عَن مَّوَاضِعِهِۦ وَيَقُولُونَ سَمِعۡنَا وَعَصَيۡنَا} [النساء: ٤٦]،

‹‹ከነዚያ ይሁዳውያን ከኾኑት ሰዎች፣ንግግሮችን ከስፍራዎቹ የሚያጣምሙ አሉ፤ሰማንም አመጥንም፣ . . ይላሉ››[አል ኒሳእ:46]

ወሰን አላፊነትንና ክፍፍሎሽን አስመልክቶም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّمَا ٱلسَّبِيلُ عَلَى ٱلَّذِينَ يَظۡلِمُونَ ٱلنَّاسَ وَيَبۡغُونَ فِي ٱلۡأَرۡضِ بِغَيۡرِ ٱلۡحَقِّ} [الشورى: ٤٢]،

‹‹(የወቀሳ) መንገዱ፣በነዚያ ሰዎችን በሚበድሉት፣በምድርም ውስጥ ያለ ሕግ ወሰን በሚያልፉት ላይ ብቻ ነው፤››[አል ሹራ:42]

ሳይንሳዊ ተአማኒነትንና በሰዎች መካከል ፍትሕ ማስፈንን አስመልክቶም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذَا حَكَمۡتُم بَيۡنَ ٱلنَّاسِ أَن تَحۡكُمُواْ بِٱلۡعَدۡلِ} [النساء: ٥٨]،

‹‹በሰዎችም መካከል በፈረዳችሁ ጊዜ፣በትክክል እንድትፈርዱ፣(ያዛችኋል)፤››[አል ኒሳእ:58]

ፍትሕ አክባሪነትን፣ማስተካከልንና በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እውነትን ብቻ መመስከርን አስመልክቶም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُونُواْ قَوَّٰمِينَ بِٱلۡقِسۡطِ شُهَدَآءَ لِلَّهِ وَلَوۡ عَلَىٰٓ أَنفُسِكُمۡ} [النساء: ١٣٥]،

‹‹እላንተ ያመናችሁ ሆይ! በትክክል (ፍትሕ) ቀዋሚዎች፣በነፍሶቻችሁ፣ . . ላይ ቢኾን እንኳ ለአላህ መስካሪዎች ኹኑ::››[አል ኒሳእ:135]

ማስረጃን ማረጋገጫንና አስረጅን ማቅረብና መመርመር አስፈላጊ መሆኑን አስመልክቶም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلۡ هَاتُواْ بُرۡهَٰنَكُمۡ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ۝٦٤} [النمل: ٦٤]،

‹‹እውነተኞች እንደ ኾናችሁ፣አስረጃችሁን አምጡ በላቸው::››[አል ነምል:64]

ከነዚህም ሌላ ለዕውቀትና ለስልጣኔው መንገድ ሳይንሳዊ ስልትን የሚያኖሩ ሌሎች ብዙ ነገሮች ይገኛሉ::

ምርጥ ሥርዓት

‹‹ዘመናት ማቅረብ የቻሉት የተሻለ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ሥርዓት በመሆኑ እስላም ድል ማድረግ ችሏል:: በደረሰበት ቦታ ሁሉ በፖለቲካ ኋላ ቀር የሆኑ፣ግፍና ምዝበራ የሚፈጸምባቸው፣በፍርሃትና በስጋት ውስጥ የሚኖሩ፣ዕውቀትም ሆነ ሥርዓት የሌላቸው ሕዝቦች ያጋጥሙት ስለነበረ እስላም መሰራጨት ችሏል:: በተመሳሳይ መልኩም ከሕዝባቸው ጋር ግንኙነት የሌላቸው ጤናማ ያልሆኑ ራስ ወዳድ መንግሥታትን ያገኝ ስለነበረም እስከዚያን ጊዜ ድረስ በዓለም ላይ የተጨባጭ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ገጽታ የነበረው፣ከሁሉም ይበልጥ ስፋት ያለው፣ይበልጥ ዘመናዊና ይበልጥ ጽዱ የሆነ ፖለቲካዊ እሳቤ ነበር:: ከማናቸውም ሌላ ሥርዓት የተሻለ ሥርዓትም ለሰው ልጆች ያቀርብ ነበር:: በሮማውያን ግዛተ አጼ የነበረው የባርያ አሳዳሪ ካፒታሊስታዊ ሥርዓት፣በአውሮፓ የነበረው ስነ ጽሑፍ፣ስልጣኔ፣ማሕበራዊ ወግና ልማድም፣እስላም ከመመስረቱ ቀደም ብሎ ከስመውና ሙሉ በሙሉ ወድመው ነበር::››

ሀርበርት ጆርጅ ዎልዝ

እንግሊዛዊ ጸሐፊና የስነጽሑፍ ሰው

የስልጣኔ መንገድ ፦

የትኛውም ሕዝብ ወይም ማህበረሰብ፣ኋላ ቀርም ይሁን ያደገ፣የራሱ የሆነ መለዮ የሚያሰጠው የሆነ ባህል የግድ ይኖረዋል:: ባህል የአነዋነዋር መንገድ፣ስለ ሕይወትና ስለ ፍጥረተ ዓለም የሚያዝ አቋም፣የሕይወት ገጽታዎችንና ነጠላ ጉዳዮችንም በጥቅሉ የሚገዛ ስነምግባራዊና ማህበራዊ እሴት ነው:: በእንቅስቃሴና በተግባር መልክ የሚገለጽ ሲሆን ለማህበረሰቡ ማንነቱን የሚያላብስ፣አንድነቱንና ትስስሩንም ጠብቆ የሚያቆይ ነው:: ስልጣኔ ግን በማህበረሰቡ ባህላዊ ሕላዌ ላይ ተጨማሪ ገላጭ የሆነ፣የዕድገትን ትርጓሜና የዓይነትና የብዛት ብልጫን የሚያመለክት፣ተጨባጭ የሆነ ስኬትን የሚያሳይ፣በታሪካዊ ስነምህዳር ላይ ግልጽ አሻራ ያለው፣ሁነቶቹን በማስገኘትና በመምራት ረገድ ከጊዜና ከቦታ አንጻር የአንጻባራቂ ለውጥና የሽግግር ወሳኝ ነጥብ እስከ መመስረት የሚደርስ ንቁ ተሳትፎ አለው:: እያንዳንዱ ስልጣኔም በዚህ መልኩ የተፈጥሮ፣የስነምህዳር፣የፖለቲካ፣የሃይማኖት፣የባህል፣የትምህርትና የስነምግባር ቅንጅትና ስብጥር ነው:: እነዚህ አለባዎች በጥምረት ተቀናጅተውና ተዋሕደው የዚህን ወይም የዚያን ሕዝብ ስልጣኔ ከልዩ መለያዎቹና መገለጫዎቹ ጋር ይመሰርታሉ::



ከግብዝነት ምልክቶች አንዱ ነው

‹‹በዚህ አንድ ዓለም ውስጥ፣ዛሬ ሙስሊምና ክርስቲያን ዐረቦች ከአውሮፓውያን ጋር ያላቸው ትስስር እየጨመረ በመጣበት በዚህ ወቅት፣እስላም በአውሮፓ ላይ ያሳደረውን ተጽእኖና የተዋቸውን አሻራዎች የሚመለከት ጥናት ይፋ መደረጉ በጣም ተገቢ ነው:: አንድ ወቅት ላይ በመካከለኞቹ ክፍለ ዘመናት የአውሮፓ ክርስቲያን ጸሐፍት በተለያዩ ጎኖች የእስላምን ገጽታ አበላሽተው ማቅረባቸው የሚታወቅ ነው:: በተገባደደው ክፍለ ዘመን ግን ተመራማሪዎች ባደረጉት ጥረት የበለጠ ተጨባጭነትና ሚዛናዊነት ያለው የእስላም ምስል በምዕራባውያን አእምሮ ውስጥ መቀረጽ ጀምሯል:: ከዐረቦችና ከሙስሊሞች ጋር መልካም ግንኙነት ይኖረን ዘንድ፣ሙስሊሞች በኛ ላይ ያላቸውን ትሩፋት ሁሉ አምነን መቀበል ይኖርብናል:: ያንን ለመካድ የምናደርጋቸው ጥረቶች ግን ራስን በውሸት ከማሞካሸትና ከግብዝነት ምልክቶች አንዱ ከመሆን አያልፍም::››

ሞንት ጎመሪ ዋት

እንግሊዛዊ ኦሪየንታሊስት

እስላም የመጀመሪያዎቹን የምእመናን ስብስብ፣ጠባብ ብሔርተኝነትና ኋላ ቀርነት ከተንሰራፋበት የዘላንነት ሕይወት በማውጣት፣ለስልጣኔና ለትሩፋት መንፈስ ስርጸት ወደሚያብቃ የመጠቀ ስነምግባርና የላቀ መርሆ ከፍ አድርጓል:: በጥቂት አስርት ዓመታት ውስጥም ሰው

https://www.path-2-happiness.com/am

ዓለም ራሷን ለውድመት አሳልፋ ስትሰጥ

‹‹ለሕይወቱ ትርጉም፣ለታሪክም ግብ ለመስጠትና ሳይንስና ሃይማኖትን የሚነጣጥለውን ምዕራባዊ ስልቱን መለወጥ ብቻ ሳይሆን በተቃራኒው አንዱ ሌላውን የሚያሟላና መከፋፈል የማይችል አንድ አሃድ አድርጎ ሁለቱን ማስተሳሰር ይችል ዘንድ፣የምዕራቡ ዓለም ከመቼውም ይበልጥ ዛሬ እስላም ያስፈልገዋል። በግለኝነቱና በራስ ወዳድነቱ መላውን ዓለም ለውድመት አሳልፎ በሚሰጥ ሁኔታ ለተበከሉት ምዕራባዊ ሕብረተሰቦቻችንም እስላም ተስፋ ሊጭር ይችላል።››

መርመዱክ ፒክትሆል

እንግሊዛዊ ጸሐፊና የስነጽሑፍ ሰው

ሳይንሳዊ ስኬቶች

‹‹እስላም ለስምንት ምእተ ዓመታት ታላላቅ ሳይንሳዊ ስኬቶችን እውን አድርጓል። በመሆኑም እስላምን የስልጣኔ አስተላላፊ ብቻ እንጂ ሰሪው አድርጎ አለመውሰድ፣ወይም የምዕራባውያንን ስልጣኔን ሙሉ በሙሉ ምዕራባዊ አድርጎ መውሰድ ስሕተት ይሆናል። እስላም የምዕራባውያን ስልጣኔ እነዚያን ስኬቶች እንዲያስመዘግብ ያስቻሉትን የመጀመሪያዎቹን መሰረቶች በመጣሉ ረገድ ትልቅ ውለታ ውሎለታል።››

ልዑል ቻርልዝ

የእንግሊዝ አልጋ ወራሽ

https://www.path-2-happiness.com/am

በሚኖርበት አብዛኛው የዓለም ክፍል በድል አድራጊነት ለመሰራጨት ችለዋል። ሙሐመድ ﷺ ይዘው የመጡት ሃይማኖት በነበረው ገርነት፣ፍትሐዊነትና እኩልነት ምክንያት እስላማዊው ስልጣኔ በወቅቱ በብዙ ሕዝቦች ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ችሏል። የእስላም ስልጣኔ ብርሃን የፈነጠቀው፣ሰዎች በባርነትና በጭቆና ላይ የተመሰረተውን የቀድሞውን ስርዓት በተሰላቹበትና በጠሉበት፣በጨቋኝ አምባገነን አጼዎች፣በአውቶክራቶች፣በቀሳውስትና ካህናት ሥርዓት ስር የግፍና የሰቆቃ ሕይወት ካንገሸገሻቸው በኋላ ሰብአዊ ክብራቸውን የሚመልስላቸውንና እንደ ሰው የሚያከብራቸውን አዲስ ሥርዓት በናፈቁበት ወቅት ላይ ነበር። ለዚህም እስላም ወርቃማ ዕድል ይዞላቸው መጣ፤የብዙዎቹን ሁኔታ በአስደናቂ ፍጥነት ሲለውጥ ሲመለከቱም የናፍቁትን ሰብአዊ ክብርና ክቡር ሕይወት ለማየት በቁ። ከግፍ ከማይምነትና ከኋላ ቀርነትም አላቀቃቸው።

እስላማዊው ስልጣኔ ለሰው ልጅ ያለው አመለካከት በሰብአዊ ክብር ላይ የተመሰረተ በመሆኑ፣አንድም ቀን ሰብአዊ ፍጡርን ከመሰሉ ሌላ ሰብአዊ ፍጡር በዘሩ፣በቆዳ ቀለሙ፣ወይም በሚናገረው ቋንቋ ምክንያት አበላልጦ አያውቅም። በጥላው ስር ሁሉም ተመሳሳይ አያያዝና እኩል መብቶችን ተጎናጽፈዋል። እስላማዊው ስልጣኔ፣በዘርና በደም ትስስር ላይ የቆመውን የጎሳ ሥርዓት፣ዐቂዳና እሳቤን በሚጋራና ማሕበራዊ ትስስሩ በወንድማማችነትና በእኩልነት ላይ

በተመሰረተ አንድ የጋራ ማሕበረሰብ ከለወጠ በኋላ፣ለሰው ልጆች ዕድገትና እርምጃ ወሳኝ የሆነ ታላቅ ድርሻ አበርክቷል።

በእስላም አመለካከት የመጀመሪያው ግብ ሰላምን መረጋጋትንና ደህንነትን ለሰው ልጆች ማረጋገጥ፣ዓይነተኛ የሆነ መልካም ሕብረተሰብ መገንባትና የሰው ልጆችን በመልካሙ ሁሉ ማስደሰት፣ክፉና እኩይ የሆነው ሁሉ መዋጋት ነው። ይኸውም በተለያዩ ገጽታዎቹ የስልጣኔ ዕድገት ማምጣት ብቻ በራሱ ተፈላጊው ግብ ባለመሆኑና የትክክለኛ ስልጣኔ ዓላማ መንፈሳዊ ደስታንና ሕሊናዊ እርካታን፣ከሰላምና ከልማት ጎን ለጎን ለሕብረተሰብና ለአገር እውን ማድረግ በመሆኑ ነው። ይህ እውን የሚሆነው በጎና ጠቃሚ የሆነውን ሁሉ በማስገኘትና ክፉና ጎጂ ከሆነው ሁሉ በማራቅ ነው።

በተጻራሪው ዘመናዊው ስልጣኔ የሰውን ልጅ እየጨመረ ለሚሄድ ጭንቀትና አለመረጋጋት የዳረገው ሲሆን፣በተንሰራፋው ቁሳዊ ጥመት ውስጥ ለመጥለቅ፣ከመልካም ስነምግባር፣ከሃይማኖትና ከሰብአዊ እሴቶችም ለመራቅ፣ኃይለኛው ደካማውን ወደሚደፍቅበት መንፈስ አልባ ግዑዝ መሳሪያነት ለመቀየር አደጋ የሰው ልጆችን አጋልጧል።

የስልጣኔ መንገድ መደላደሎች

እስላማዊው ስልጣኔ ግን ጉልህ በሆኑ መለያዎቹና ልዩ በሆኑ ባሕርያቱ ሌሎች ስልጣኔዎች የሚጋሩት የተወሰኑ ጉዳዮች ቢኖሩም የስልጣኔ መሰረትቶችን፣ግቦቹንና መርሆዎቹን በተመለከተ የራሱ የሆነ ነጻ ገጽታዎችና መገለጫዎች ያሉት ምሉእ ማንነት ያለው ስልጣኔ ነው።

የእስላም ስልጣኔ መሰረት፣በግሪኮች ዘንድ እንዳለው ዓይነት አእምሮን ከገደብ ባለፈ ሁኔታ አግንኖ ማምለክ አይደለም። ሮማውያን ዘንድ እንደ ነበረው በስልጣን፣በኃይልና በተጽእኖ አምላኪነት ላይ የተመሰረተም አይደለም። በፋሪሳውያን ዘንድ እንደ ነበረው በሥጋዊ ደስታዎች፣በብርቱ ጦረኝነትና በፖለቲካዊ አቅም ላይ የሚያተኩርም አይደለም። በሕንዶችና በከፊል ቻይናውያን ዘንድ እንደ ነበረው በመንፈሳዊ ኃይል በመመካት ላይ የታነጸም አይደለም። በመካከለኛው ክፍለ ዘመን አውሮፓን ለድቅድቅ የማይምነት ጨለማ በዳረገውና በአፈ ታሪክና በቅዠት ላይ የተመሰረተው የመነኮሳትና የካህናት የእብሪት

መካከለኞቹ ክፍለ ዘመናት

‹‹ሙሳ ብን ኑሰይር አውሮፓን ማቋረጥ ተሳክቶለት ቢሆን ኖሮ አውሮፓን ሙስሊም ባደረጋት ነበር፤ለሰለጠኑ ሕዝቦችም ሃይማኖታዊ አንድነትን ማስገኘት በቻለ ነበር። በዐረቦች ምክንያት እስፔን ሳይደርስባት ካመለጠችው የመካከለኞቹ ክፍለ ዘመናት ሁኔታ አውሮፓንም መታደግ በቻለ ነበር።››

ጉስታፍ ሊቦን

ፈረንሳዊ ታሪክ ጸሐፊ

https://www.path-2-happiness.com/am

ተሸናፊ አሸናፊውን ማረከው!!

‹‹በመስቀል ጦርነቶች ተሸናፊው እስላም አሸናፊዎቹን ማርኳል። የዛገ ላቲናዊ ሕይወት ወደነበረው ወደ ክርስቲያኑ ዓለም ሕይወትም የስልጣኔ ዓይነቶችን አስገብቷል። በአንዳንድ ሰብአዊ እንቅስቃሴ መስኮች፣ለምሳሌ በኪነ ሕንጻ በመካከለኞቹ ክፍለ ዘመናት እስላማዊው ተጽእኖ በመላው የክርስቲያን ዓለም ስር የሰደደ ነበር። በሲስሊና በአንደሉስ ደግሞ ጥንታዊው ዐረባዊ ኢምፓይር በአዲሱ ምዕራባዊ መንግስት ላይ ያሳረፈው አሻራ ሰፊ፣ጥልቅና አጠቃላይ ነበር።››

አርኖልድ ቱዌንቢ
እንግሊዛዊ ታሪክ ጸሐፊ

ኃይልና ተጽእኖ ላይ የተመረኮዘም አይደለም። ከግሪክና ከሮማውያን ስልጣኔ እንደ ተወረሰውና በቁሳዊ ዕውቀት ላይ በመመካት የምድረ ዓለሙን እምቅ ሀብት በመዝረፍ ላይ እንደ ቆመው ዘመነኛው የአውሮፓ ስልጣኔም አይደለም። እስላማዊ ስልጣኔ የተመሰረተው በተውሒድ፣በርእዮት፣ሰብአዊ ክብርን በማረጋገጥና ሁሉንም የሰው ልጅ የሕወት ፈርጆች በሚዳስስ እውነታ ላይ ነው። በዚህም እስላማዊው ስልጣኔ ራሱን የቻለና የተሟላ፣አጠቃላይነት ያለው ሕግና ሥርዓት ባለቤት የሆነ፣ከተቀሩት ሌሎች ስልጣኔዎች መርሆዎች ጋር መሰረታዊ የሆነ ልዩነት ያለው ስልጣኔ ነው። እስላማዊው ስልጣኔ እውስጡ በያዘው የትግልና የተጋድሎ፣የፍትሕና የርትዕ፣ከተቃራኒ ጋር ተቻችሎ በመኖር፣ለመላው የሰው ዘር ደግ ደጉን በመውደድና በመስራት፣ዕውቀትና ጥበብን በማሰራጨት . . ረገድ ባለው እምቅ ኃይልና የመንፈስ ጥንካሬ በሌሎች ላይ የበላይነትን የተቀዳጀ ስልጣኔ ነው። ስለሆንም በእጁ ካለው ታላቅ ጥሪትና እምቅ ስንቅ አንጻር ዳግም የሰው ልጆችን አመራር ለመረከብ የታጨ ድንቅ ስልጣኔም ነው።

እስላማዊ ስልጣኔ የራሱ የሆኑ አያሌ መለያዎችና መገለጫዎች አሉት፤ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ፦

1- ኢማንና ተውሒድ ፦

ኢማን የደስተኝነት መንገድ ስረ መሰረትና ለዕውቀት ግብይትና ለስልጣኔ ምስረታ ዋነኛው ግፊት ፈጣሪ ተደርጎ ይወሰዳል። በአላህ በማመንና አንድነቱን በማረጋገጥ ላይ ያልተመሰረተ ማንኛውም ስልጣኔ፣በውስጣዊ ቅራኔና ግጭት የታጨቀ፣እርሱ በርሱ አንዱ ክፍል ሌላውን የሚያፈርስ፣የሰውን ልጅ ሕይወት በማበላሸት ወደ አለመታደል የሚወስዱትና የተለያዩ ስሞች ተሰጥቷቸው የሚመለኩ አማልክት የሚመለኩበት ስልጣኔ ነው!! አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لَوۡ كَانَ فِيهِمَآ ءَالِهَةٌ إِلَّا ٱللَّهُ لَفَسَدَتَاۚ فَسُبۡحَٰنَ ٱللَّهِ رَبِّ ٱلۡعَرۡشِ عَمَّا يَصِفُونَ ﴿٢٢﴾} [الأنبياء: ٢٢]،

‹‹በሁለቱ (በሰማያትና በምድር) ውስጥ ሌላ አማልክት በነበሩ ኖሮ፣በተበላሹ ነበር፤የዐርሹ ጌታ አላህም ከሚሉት ሁሉ ጠራ።››[አል አንቢያ፡22]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{مَا ٱتَّخَذَ ٱللَّهُ مِن وَلَدٖ وَمَا كَانَ مَعَهُۥ مِنۡ إِلَٰهٍۚ إِذٗا لَّذَهَبَ كُلُّ إِلَٰهِۭ بِمَا خَلَقَ وَلَعَلَا بَعۡضُهُمۡ عَلَىٰ بَعۡضٖۚ سُبۡحَٰنَ ٱللَّهِ عَمَّا يَصِفُونَ ﴿٩١﴾} [المؤمنون:٩١]

‹‹አላህ ምንም ልጅን አልያዘም (አልወለደም)፤ከርሱም ጋር አንድም አምላክ የለም፤ያን ጊዜ፣(ሌላ አምላክ በነበረ)፣አምላክ ሁሉ በፈጠረው ነገር በተለየ ነበር፤ከፊላቸውም በከፊሉ ላይ በላቀ ነበር፤አላህ ከሚመጥኑት ሁሉ ጠራ።››[አል ሙእሚኑን፡91]

በተጨማሪም (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُل لَّوۡ كَانَ مَعَهُۥٓ ءَالِهَةٞ كَمَا يَقُولُونَ إِذٗا لَّٱبۡتَغَوۡاْ إِلَىٰ ذِي ٱلۡعَرۡشِ سَبِيلٗا ﴿٤٢﴾} [الإسراء:٤٢]

‹‹(ሙሐመድ ሆይ) በላቸው ፦ እንደምትሉት ከርሱ ጋር አማልክት በነበሩ ኖሮ ያን ጊዜ ወደ ዐርሹ (ወደ ዙፋኑ) ባለቤት መንገድን በፈለጉ ነበር።›› [አል እስራእ፡42]

የዚህ ነፀብራቅ በብዙዎቹ ስልጣኔዎች ላይ የደረሰውና በመድረስ ላይ የሚገኘው ሲሆን፣መድረስ ከፈለጉበት ግባቸው ተዛንፈው፣ዓላቸውን ስተው በጎ አስበው ቢሆን እንኳ ለሰው ልጆች ያለመታደልና ለጥፋት መንስኤ ሆነዋል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱتَّخَذُوٓاْ أَحۡبَارَهُمۡ وَرُهۡبَٰنَهُمۡ أَرۡبَابٗا مِّن دُونِ ٱللَّهِ وَٱلۡمَسِيحَ ٱبۡنَ مَرۡيَمَ وَمَآ أُمِرُوٓاْ إِلَّا لِيَعۡبُدُوٓاْ إِلَٰهٗا وَٰحِدٗاۖ لَّآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۚ سُبۡحَٰنَهُۥ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ﴿٣١﴾} [التوبة: ٣١].

‹‹ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለውን አንድን አምላክ ሊግገዙ እንጂ ያልታዘዙ ሲኾኑ፣ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸውን፣የመርየምን ልጅ

በያንዳንዱ የሕይወት ዝርዝር ይገባል!!

‹‹እስላም ለሰው ልጆች ተመራጩ ሃይማኖት ነው። እስላም በያንዳንዲቱ የሙስሊም ሰው ሕይወት ዝርዝር ውስጥ ዘልቆ መግባት ብቻ ሳይሆን፣አንድ ሙስሊም በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ሁሉ የወሳኝነት ሚና አለው። በዛሬው ዓለም ላይ ከእስላም በስተቀር ሁሉንም የሰው ልጆች ችግር የመፍታት አቅም ያለው አንድም ሌላ ሃይማኖት አይገኝም። ይህ የእስላም ብቻ ሆነ ልዩ መለያው ነው።››

ኮፍሂ ላል ጃባ
ሕንዳዊ ፖለቲከኛና ጋዜጠኛ



ተገቢው መሪ ዬት አለ?!

‹‹ስለ እስላም ተገቢውን ንግግር የሚናገር ተገቢው መሪ ከተገኘ፣ይህ ሃይማኖት ከመሰረታዊ ኃያላን ኃይሎች አንዱ ሆኖ በድጋሚ መውጣት ይችላል።››

ሞንት ጎመሬ ዋት
እንግሊዛዊ ኦሪየንታሊስት

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

አልመሲሕንም፣ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ፤ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ ነው፡፡››[አል ተውበህ:31]

2- ዓለም አቀፋዊነት ፦

እስላም ለሁሉም ዘመንና ስፍራ፣ለሁሉም የሰው ዘርና ቋንቋ፣ለሁሉም የቆዳ ቀለምና ዝርያ የመጣ ዓለም አቀፋዊ ሃይማኖት ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا كَآفَّةٗ لِّلنَّاسِ بَشِيرٗا وَنَذِيرٗا وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعۡلَمُونَ ٢٨} [سبأ: ٢٨]،

‹‹አንተንም ለሰዎች ሁሉ በመላ፣አብሳሪና አስፈራሪ አድርገን ቢኾን እንጂ አልላክንህም፤ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም፡፡››[ሰበእ፡28]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{تَبَارَكَ ٱلَّذِي نَزَّلَ ٱلۡفُرۡقَانَ عَلَىٰ عَبۡدِهِۦ لِيَكُونَ لِلۡعَٰلَمِينَ نَذِيرًا ١} [الفرقان: ١]،

‹‹ያ ፉርቃንን (ውነትን ከውሸት የሚለየውን መጽሐፍ፣ቁርኣንን) በባሪያው ላይ፣ለዓለማት አስፈራሪ [አስጠንቃቂ] ይኾን ዘንድ ያወረደው (አምላክ)፣ክብርና ጥራት ተገባው፡፡››[አል ፉርቃን፡ 1]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلۡ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنِّي رَسُولُ ٱللَّهِ إِلَيۡكُمۡ جَمِيعًا ٱلَّذِي لَهُۥ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ}[الأعراف: ١٥٨]،

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው ፦ እላንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደ ሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ፤(እርሱም) ያ የሰማያትና የምድር ንግሥና ለርሱ ብቻ የኾነ ነው፤››[አል አዕራፍ፡158]

በተጨማሪም (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا رَحۡمَةٗ لِّلۡعَٰلَمِينَ ١٠٧} [الأنبياء: ١٠٧]،

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም፡፡››[አል አንቢያ፡107]

እስላም የመጣው በሁኔታዎች መለዋወጥ የማይለወጥ ቋሚ ዐቂዳ፣በሁሉም ዘመንና ስፍራ ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ጋር የተጣጣመ የፍትሕ፣ የእውነትና የበጎነት መርህ ላይ የተመሰረተ ሸሪዓ (ድንጋጌ) ይዞ ነው፡፡ ይህ የሆነው ለፍጡራኑ የሚበጀውንና የሚጠቅማቸውን ከሚያውቀው አላህ (ሱ.ወ.) ዘንድ

‹‹የተላክሁት ከእስራኤል ቤት ሆነው ወደ ጠፉት በጎች ብቻ ነው፡፡›› አስራ ሁለቱን መርጦ ወደ አይሁዶች ሲልካቸው እንዲህ በማለት ነበር ያዘዛቸው፦ ‹‹ወደ አሕዛብ አትሂዱ፤ወደ ሳምራውያን ከተማም አትግቡ፡፡ ይልቁንስ የእስራኤል ቤት ወደሆኑት ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ፡፡››

የማቴዎስ ወንጌል



የመጣ በመሆኑ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦\

{أَلَا يَعۡلَمُ مَنۡ خَلَقَ وَهُوَ ٱللَّطِيفُ ٱلۡخَبِيرُ ١٤}[الملك: ١٤]،

‹‹የፈጠረ አምላክ እርሱ ዕውቀተ ረቂቁ፣ውስጠ ዐዋቂው ሲኾን፣(ምስጢርን ሁሉ) አያውቅምን?››[አል ሙልክ፡14] እስላም የመጣው በሁኔታዎች መለዋወጥ የማይለወጥ ቋሚ ዐቂዳ፣በሁሉም ዘመንና ስፍራ ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ጋር የተጣጣመ የፍትሕ፣ የእውነትና የበጎነት መርህ ላይ የተመሰረተ ሸሪዓ (ድንጋጌ) ይዞ ነው፡፡ ይህ የሆነው ለፍጡራኑ የሚበጀውንና የሚጠቅማቸውን ከሚያውቀው አላህ (ሱ.ወ.) ዘንድ የመጣ በመሆኑ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَلَا يَعۡلَمُ مَنۡ خَلَقَ وَهُوَ ٱللَّطِيفُ ٱلۡخَبِيرُ ١٤}[الملك: ١٤]،

‹‹የፈጠረ አምላክ እርሱ ዕውቀተ ረቂቁ፣ውስጠ ዐዋቂው ሲኾን፣(ምስጢርን ሁሉ) አያውቅምን?››[አል ሙልክ፡14]

እስላም ለተወሰነ ቡድን ወይም ስብስብ፣ለተለየ የቆዳ ቀለም፣ዘር ወይም ብሔር፣የመጣ ሃይማኖት ሳይሆን ለነጩና ለጥቁሩም፣ለብጫውና ለቀዩም የመጣ ነው፡፡ ጥንት ለነበረው፣ዛሬ ላለውና ወደፊት ለሚመጣውም መላው የሰው ልጅ ነው፡፡ ያሻውን ያህል የዕውቀትና የምርምር አቅም ያለው ተመራማሪ፣የእስላም ነቢይ ﷺ ይዘው በመጡት ሃይማኖት ውስጥ፣ክልላዊ ወይም ቡድናዊ ባህሪ፣የጎጠኛነት ወይም የዘረኛነት አዝማሚያ፣የአድልዖ ወይም የጭፍን ወገንተኝነት ይዘት ያለው አንዳች ነገር ማግኘት ፈጽሞ አይችልም፡፡ ይህም የእስላም አምልኮተ አላህ (ዕባዳ) ሥርዓት፣ሕግጋቱ፣ድንጋጌዎቹና የሞራል ሥርዓቱ ለመላው የሰው ዘር በሁሉም ጊዜና ስፍራ ምቹ የተደረጉ በመሆናቸው፣ጥሪያቸው የተወሰነ ቡድን ወይም ጎጥን ዒላማ ያላደረገ፣ለተለየ ሕዝብም ያልወገነ ዓለም አቀፋዊ ጥሪ ነው፡፡

በተለይ የእስላም በመሆኑ፣ፍትሕ ወይም መልካም ስነምግባር ለአንድ ሕዝብ ወይም ለአንድ ዘመን አይበጅም ማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በአንዳንድ ሃይማኖቶች ዘንድ ግን የክልላዊነት፣የቡድናዊነት፣ወይም የዘረኝነት

ግንባታና ልማት

‹‹እስላም ለሰላ አእምሮ፣ለመጠቀ እሳቤና ለግለሰባዊ ብቃት ዕውቅና ይሰጣል፡፡ የግንባታና የልማት ሃይማኖት እንጂ የጥፋት ሃይማኖት አይደለም፡፡ ለምሳሌ ያህል መሬት ያለው አንድ ሰው በቂ ሀብት ስላለው መሬቱን ማረስና ማልማት ባለመፈለጉ ጠፍ አድርጎ ቢተወው፣እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ሁኔታው በዚህ ከቆየ በኋላ ባለቤትነቱ ወደ ሕዝብ ይዞታነት በቀጥታ ይዛወራል፡፡ የእስላም ሸሪዓም የዚህ ዓይነቱ ጠፍ መሬት ይዞታ መጀመሪያ መሬቱን ለማረስ ወደሚሰማራው ሰው እንደሚተላለፍ ይደነግጋል፡፡››

ሴር ቻርልዝ ኤድዋርድ አርሺባልድ

እንግሊዛዊ ፖለቲከኛ

አቋም በግልጽና በግላጭ ይስተዋላል:: ለአብነት ያህል አይሁዶች ከሃይማኖታቸው ውጭ ካለው ሰው ጋር የሚኖራቸው በይነሰባዊ ግንኙነት ከይሁዳዊው ጋር ከሚኖራቸው የተለየና ከፍትሕ የራቀ ዘረኛ ግንኙነት ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) ይህን በማስመልከት እንዲህ ብሏል፦አላህ (ዕባዳ) ሥርዓት፣ሕግጋቱ፣ድንጋጌዎቹና የሞራል ሥርዓቱ ለመላው የሰው ዘር በሁሉም ጊዜና ስፍራ ምቹ የተደረጉ በመሆናቸው፣ጥሪያቸው የተወሰነ ቡድን ወይም ጎጥን ዒላማ ያላደረገ፣ለተለየ ሕዝብም ያልወገነ ዓለም አቀፋዊ ጥሪ ነው::

በተለይ የእስላም በመሆኑ፣ፍትሕ ወይም መልካም ስነምግባር ለአንድ ሕዝብ ወይም ለአንድ ዘመን አይበጅም ማለት የሚቻል አይደለም:: በአንዳንድ ሃይማኖቶች ዘንድ ግን የክልላዊነት፣የቡድናዊነት፣ወይም የዘረኝነት አቋም በግልጽና በግላጭ ይስተዋላል:: ለአብነት ያህል አይሁዶች ከሃይማኖታቸው ውጭ ካለው ሰው ጋር የሚኖራቸው በይነሰባዊ ግንኙነት ከይሁዳዊው ጋር ከሚኖራቸው የተለየና ከፍትሕ የራቀ ዘረኛ ግንኙነት ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) ይህን በማስመልከት እንዲህ ብሏል፦

{وَمِنْ أَهْلِ ٱلْكِتَـٰبِ مَنْ إِن تَأْمَنْهُ بِقِنطَارٍ يُؤَدِّهِۦٓ إِلَيْكَ وَمِنْهُم مَّنْ إِن تَأْمَنْهُ بِدِينَارٍ لَّا يُؤَدِّهِۦٓ إِلَيْكَ إِلَّا مَا دُمْتَ عَلَيْهِ قَآئِمًا ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ قَالُوا۟ لَيْسَ عَلَيْنَا فِى ٱلْأُمِّيِّـۧنَ سَبِيلٌ وَيَقُولُونَ عَلَى ٱللَّهِ ٱلْكَذِبَ وَهُمْ يَعْلَمُونَ ﴿٧٥﴾} [آل عمران: ٧٥]

.‹‹ከመጽሐፉ ሰዎችም በብዙ ገንዘብ ብታምነው ወዳንተ የሚመልስ ሰው አልለ:: ከነርሱም በአንድ ድናር እንኳ ብታምነው፣ሁልጊዜ በርሱ ላይ የምትጠባበቅ ካልኾንክ በስተቀር የማይመልስ ሰው አልለ:: ይኸ በመሃይምናን (በምናደርገው) በኛ ላይ ምንም መንገድ የለብንም ስለሚሉ ነው፤እነርሱ እያወቁም በአላህ ላይ ውሸትን ይናገራሉ::››[ኣሊ ዒምራን:75]

ነፍስን መግራት

‹‹ሳይንሳዊ ግኝቶችን እውን ለማድረግ እስላም ከሃይማኖቶች ሁሉ ይበልጥ የተመቻቸ ሃይማኖት ነው:: ነፍስን ለመግራትና ስነምግባርን በማነጽ ፍትሕና ደግነትን ለማስፈን በማስቻልም ከሁሉም ታላቁ ሃይማኖት ነው::››

ጉስታፍ ሊቦን

ፈረንሳዊ ታሪክ ጸሐፊ

በይፋና በአደባባይ

‹‹እኔ የታላቁ አገራዊ መሪ የጋንዲ ልጅ መሆኔን ሁላችሁም ታውቃላችሁ:: እነሆ በይፋና በአደባባይ በዚህ ግዙፍ የሙስሊሞች ስብስብ መካከል ሆኜ እስላምን ማፍቀሬንና ቁርኣንን መውደዴን አውጃለሁ:: በአንድ አላህና በብጹሑ መልክተኛ በመሪያችን በሙሐመድ ﷺ አምኛለሁ:: የነቢያት መደምደሚያ መሆናቸውንና ከርሳቸው በኋላ ነቢይ አለመኖሩን፣ቁርኣን ውስጥ የተካተተው ሁሉ እውነት መሆኑን፣ከአላህ የተላለፉ መለኮታዊ መጽሐፎች ሁሉ እውነት መሆናቸውን፣የአላህ ነቢያትና መልክተኞችም እውነት መሆናቸውን አምናለሁ:: ለእስላምና ለቁርኣን ብዬ እኖራለሁ፤እሞታለሁም::እ ከላከልላቸዋለሁ፤እታገላለሁም፤ከታላላቅ ዋልታዎቹም አንዱ እሆናለሁ፤አብሳሪውም እሆናለሁ:: ሕዝቤንና ወገኖችን ወደርሱ እጠራለሁ:: ይህ ሚዘናዊ ሃይማኖት የዕውቀት፣የስልጣኔ፣የፍትሕ፣የታማኝነት፣የርህራሄና የእኩልነት ሃይማኖት ነው::››

ዐብዱላህ ሄራል ጋንዲ

የማህተማ ጋንዲ ልጅ

3-የዕውቀት የግንባታና የልማት ስልጣኔ ፦

እስላም ስለ ሰው ልጅ ያለው አመለካከት ምድርን ያለማትና ያቀናት ዘንድ አላህ (ሱ.ወ.) ምትክ ወይም ኸሊፋ አድርጎ የፈጠረው መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{هُوَ أَنشَأَكُم مِّنَ ٱلْأَرْضِ وَٱسْتَعْمَرَكُمْ فِيهَا} [هود: ٦١]،

‹‹እርሱ ከምድር ፈጠራችሁ፤በውስጧ እንድታለሟት ም አደረጋችሁ፤››[ሁድ:61]

በተጨማሪም (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{هُوَ ٱلَّذِى جَعَلَكُمْ خَلَـٰٓئِفَ فِى ٱلْأَرْضِ ۚ فَمَن كَفَرَ فَعَلَيْهِ كُفْرُهُۥ ۖ وَلَا يَزِيدُ ٱلْكَـٰفِرِينَ كُفْرُهُمْ عِندَ رَبِّهِمْ إِلَّا مَقْتًا ۖ وَلَا يَزِيدُ ٱلْكَـٰفِرِينَ كُفْرُهُمْ إِلَّا خَسَارًا ﴿٣٩﴾} [فاطر: ٣٩]،

‹‹እርሱ ያ በምድር ውስጥ ምትኮች ያደረጋችሁ ነው፤የካደም ሰው ክሕደቱ በርሱ ላይ

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ብቻ ነው፤ከሃዲዎችንም ክሕደታቸው ከጌታቸው ዘንድ መጠላትን እንጅ ሌላ አይጨምርላቸውም፤ከሓዲዎችንም ክሕደታቸው ኪሳራን እንጂ ሌላ አይጨምርላቸውም::››[ፋጢር፡39]

በእስላም ሃይማኖት የሰው ልጆችን የሚጠቅምና ምድርን የሚያለማ ዕውቀት መማር ከተውና የተወሰነ ሰው ካልተማረው ሁሉም ሙስሊሞች ኃጢአተኛ ይሆናሉ:: ሙሐመድ ﷺ ሲላኩ የሰው ልጆች በስልጣኔና በዕውቀት መስክ በከፋ ኂላ ቀርነት ውስጥ ይኖሩ የነበረ ሲሆን፣ሰዎች ምድርን ለጥቅማቸው ከመግራትና ከግንባታ ርቀው በፍልስፍና ጉዳዮችና በፍሬ ቢስ ክርክሮች ተጠምደው ነበር:: ነቢዩ ﷺ የሰውን ልጅ ከዚህ ዓይነቱ አረንቋ አውጥተው የስልጣኔ፣የግንባታና የልማት ሃይማኖት በሆነው እስላም አማካይነት፣በግንባታ በመንፈስ ንጽሕና እና ምጥቀት መካከል ግጭትና ቅራኔ ሳይኖር፣አምልኮተ አላህና ልማታዊ ግንባታ በሙስሊሙ አእምሮ ውስጥ ምንም ቅራኔ ሳይፈጥሩ፣በመንፈሳዊ ሕይወቱና በሥራው መካከል የአላህን ውዴታ በማትረፍ ረገድ ምንም ግጭት ሳይኖር ብቻ ሳይሆን ይህ ሁሉ በጥምረት ለአላህ ተብሎ በርሱ መንገድ በሚሰራበት ሁኔታ ወደ ለእላይ ደረጃ ከፍ አደረጉት:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحْيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ١٦٢} [الأنعام: ١٦٢].

‹‹ስግደቴ፣መገዛቴም፣ሕይወቴም፣ሞቴም፣ለዓለማት ጌታ ነው በል::››[አል አንዓም፡162]

4- የስነምግባር ስልጣኔ ፦

መልካም ስነምግባርና ጥሩ ጠባይ እስላም ውስጥ ዕባዳ ወይም አምልኮተ አላህ ነው:: ነቢዩ ﷺ የተላኩበት ዓላማ መልካም ስነምግባራትን የተሟሉ ማድረግ መሆኑን ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹የተላክሁት መልካም ስነምግባራትን ምሉእ ለማድረግ ነው::››[በማሊክ የተዘገበ] በመሆኑም የደስተኙነትና የመታደል መንገድ መልካም ስነምግባርን ሚያበረታታ የምግባረ ሰናይነትና የምስጉን ሥራዎች መንገድ ነው:: መልካም ስነምግባር እስላም ውስጥ ሰው ከገዛ ራሱ ጋር፣ከአላህ ጋርና ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነትና የመሳሰሉትን ሁሉንም የሕይወት ፈርጆች ያጠቃልል:: ከሙስሊምም ሆነ ከካፍር፣ከትንሹም ሆነ ከትልቁም፣ከወንዱም ሆነ ከሴትዋ፣ከደጋፊውም ሆነ ከተቃዋሚው . . ከሁሉም ጋር የሚኖረውን ግንኙነትና አያያዝም ያካትታል:: እስላም ለደግነት፣ለጀግንነት፣ለፍትሕ፣ለር ህራሄ፣ለትህትና፣ለተገራ ጠባይ፣ለእውነተኛነት፣ለይሉኝታ፣ለትዕግስት፣ለቅን ልቦና፣በጎ በጎውን ለመውደድ . . ጥሪ ያደርጋል:: አላህ (ሱ.ወ.) ከተቃዋሚ ጋር ቢሆን እንኳ ፍርድ ማስተካከልና ፍትሐዊ መሆን ግዴታ መሆኑን ሲያረጋግጥ እንዲህ ብሏል፦

{يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُونُواْ قَوَّٰمِينَ لِلَّهِ شُهَدَآءَ بِٱلْقِسْطِ وَلَا يَجْرِمَنَّكُمْ شَنَـَٔانُ قَوْمٍ عَلَىٰٓ أَلَّا تَعْدِلُواْ ٱعْدِلُواْ هُوَ أَقْرَبُ لِلتَّقْوَىٰ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ إِنَّ ٱللَّهَ خَبِيرُۢ بِمَا تَعْمَلُونَ ٨} [المائدة: ٨]،

‹‹እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ለአላህ ቀጥተኞች፣በትክክል መስካሪዎች ኹኑ:: ሕዝቦችንም መጥላት፣ባለማስተካከል ላይ አይገፋፋችሁ፤አስተካክሉ፤እርሱ (ማስተካከል) ለአላህ ፍራቻ በጣም የቀረበ ነው:: አላህንም ፍሩ:: አላህ በምትሠሩት ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው::›[አል ማኢዳህ፡8]

የነቢዩ ሙሐመድን ﷺ መልእክት አስመልክቶ በርሳቸው አምኖ በተከተላቸው ላይ ብቻ ሳይወሰን ለዓለማት ሁሉ እዝነትና ጸጋ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ أَرْسَلْنَٰكَ إِلَّا رَحْمَةً لِّلْعَٰلَمِينَ ١٠٧}[الأنبياء: ١٠٧]،

‹‹(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም::››[አል አንቢያ፡107]

ይህ ስነምግባር ከእስላማዊ ስልጣኔ ዐቢይ ክፍል ተለይቶ የማይወጣ አንድ አካሉ ብቻ ሳይሆን ዋነኛ ማእዘኑም ጭምር ነው:: ምስጉን ባህርያት በሥራና በግንባታ ወይም በሌላ ማንኛውም ጥቅም ወይም በሌላ ማንኛውም ምክንያት ከአንድ ሙስሊም ፈጽሞ መራቅ አይችልም:: አላህ (ሱ.ወ.) የርሱን ነቢይ የሙሐመድን ﷺ ለኛ የመልካም ስነ ምግባርና የምስጉን ባሕርያት አርአያችን ይሆኑ ዘንድ ስነምግባራቸውን ገርቷል:: አላህ (ሱ.ወ.) ይህን በማስመልከት እንዲህ ብሏል፦

{لَّقَدْ كَانَ لَكُمْ فِي رَسُولِ ٱللَّهِ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ لِّمَن كَانَ يَرْجُواْ ٱللَّهَ وَٱلْيَوْمَ ٱلْأَخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرًا ٢١} [الأحزاب: 21].

‹‹ለናንተ፣አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለኾነ ሰው፣አላህንም በብዙ ለሚያወሳ፣በአላህ መልክተኛ መልካም መከተል አላችሁ::››[አል አሕዛብ፡21]

ከነቢዩ ﷺ እዝነት፣ከርህራሄያቸውና ሰዎችን ወደ መታደል መንገድ ለመምራት ካላቸው ጉጉት ከፊሉን ሲገልጽ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لَقَدْ جَآءَكُمْ رَسُولٌ مِّنْ أَنفُسِكُمْ عَزِيزٌ عَلَيْهِ مَا عَنِتُّمْ حَرِيصٌ عَلَيْكُم بِٱلْمُؤْمِنِينَ رَءُوفٌ رَّحِيمٌ ١٢٨} [التوبة: ١٢٨].

‹‹ከጎሳችሁ የኾነ፣ችግራችሁ በርሱ ላይ ጥኑ የኾነ፣በናንተ (እምነት) ላይ የሚጓጓ፣በምእመናን ርኅሩህ አዛኝ የኾነ መልክተኛ በእርግጥ መጣላችሁ::››[አል ተውበህ፡128]

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

5 - የአእምሮና የእሳቤ ስልጣኔ ፦

በእስላም ሃይማኖት ውስጥ ጥያቄ የማይቀርብበትና የማይመረመር ምንም ዓይነት ክህነታዊ ምስጢር የለም። ይልቅዬ አላህ (ሱ.ወ.) ሰዎች ስለ ተአምራቱ፣ስለ ፍጥረታቱና ስለ ሕዝቦች ሁኔታ እንዲያስተነትኑ እና እንዲመራመሩ በማዘዝ እንዲህ ብሏል፦

{ٱلَّذِينَ يَذْكُرُونَ ٱللَّهَ قِيَٰمًا وَقُعُودًا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمْ وَيَتَفَكَّرُونَ فِى خَلْقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ رَبَّنَا مَا خَلَقْتَ هَٰذَا بَٰطِلًا سُبْحَٰنَكَ فَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ﴿١٩١﴾} [آل عمران: ١٩١]،

‹‹(እነርሱም) እነዚያ ቆመው ተቀምጠውም፣በጎኖቻቸው ተጋድመውም፣አላህን የሚያወሱ፣በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም የሚያስተነትኑ ፦ ጌታችን ሆይ! ይኸን በከንቱ አልፈጠርከውም፤ጥራት ይገባህ፤ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን የሚሉ ናቸው።››[ኣሊ ዒምራን:191]

በተጨማሪም (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{كَذَٰلِكَ نُفَصِّلُ ٱلْءَايَٰتِ لِقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ ﴿٢٤﴾} [يونس: ٢٤]،

‹‹እንደዚሁም ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች አንቀጾችን እናብራራለን።››[ዩኑስ:24]

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{بِٱلْبَيِّنَٰتِ وَٱلزُّبُرِ ۗ وَأَنزَلْنَآ إِلَيْكَ ٱلذِّكْرَ لِتُبَيِّنَ لِلنَّاسِ مَا نُزِّلَ إِلَيْهِمْ وَلَعَلَّهُمْ يَتَفَكَّرُونَ ﴿٤٤﴾} [النحل: ٤٤]،

‹‹በግልጽ ማስረጃዎችና በመጻሕፍት (ላክናቸው)፤ወደ አንተም፣ለሰዎች ወደነሱ የተወረደውን (ፍች) ልትገልጽላቸውና ያስተነትኑም ዘንድ ቁርኣንን አወረድን።››[አል ነሕል:44]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَوَلَمْ يَتَفَكَّرُوا۟ فِىٓ أَنفُسِهِم ۗ مَّا خَلَقَ ٱللَّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَمَا بَيْنَهُمَآ إِلَّا بِٱلْحَقِّ وَأَجَلٍ مُّسَمًّى ۗ وَإِنَّ كَثِيرًا مِّنَ ٱلنَّاسِ بِلِقَآئِ رَبِّهِمْ لَكَٰفِرُونَ ﴿٨﴾} [الروم: ٨]،

‹‹በነፍሶቻቸው (ኹኔታ) አያስተነትኑምን? ሰማያትንና ምድርን፣በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ፣አላህ በውነትና በተወሰነ ጊዜ እንጂ አልፈጠራቸውም፤ከሰዎቹም ብዙዎቹ በጌታቸው መገናኘት ከሓዲዎች ናቸው።››[አል ሩም:8]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَتِلْكَ ٱلْأَمْثَٰلُ نَضْرِبُهَا لِلنَّاسِ لَعَلَّهُمْ يَتَفَكَّرُونَ ﴿٢١﴾}[الحشر: ٢١]،

‹‹ይህችንም ምሳሌ ይገመግሙ ዘንድ ለሰዎች እንገልጻታለን።››[አል ሐሽር:21]

ከዚህም በላይ አላህ (ሱ.ወ.) ዕውቀት እንዳው በግምትና በይሆናል ሳይሆን የግድ ማስረጃ ሊቀርብበት እንደሚገባ ያስተምረናል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ هَاتُوا۟ بُرْهَٰنَكُمْ إِن كُنتُمْ صَٰدِقِينَ ﴿١١١﴾} [البقرة: ١١١]،

‹‹እውነተኞች እንደኾናችሁ፣አስረጃችሁን አምጡ በላቸው።››[አል በቀራህ:111]

የሃይማኖት መሪዎችና ካህናት ብቻ እንጂ ሌላው የማያውቀው ነገርም ሆነ ሊፈታ የማይችል ምንም ዓይነት ሃይማኖታዊ ምስጢርና እንቆቅልሽ እስላም ውስጥ ለም።

6- የውስጣዊና ውጫዊ ሰላም እርካታ ስልጣኔ፦

ውስጣዊ ሰላምና መረጋጋት ማለት፣በዘመናችን ስልጣኔ ውስጥ ብዙዎችን ከሚያናውጡ ውስጣዊ ግጭቶች፣የዱንያ ዓለማዊ ሕይወቱና የወዲያኛው የኣኽራ ሕይወቱ በአእምሮውና በሕሊናው ውስጥ ተጣጥመው በሚገኙበት ሁኔታ የሰው ልጅ ነጻ ሆኖ በተረጋጋ መንፈስ በሰላም መኖር ማለት ነው። አምልኮተ አላህ ከሥራና ከግንባታ ጋር የሚጣመርበት፣የመንፈስና የሥጋ ፍላጎት የሚጣጣምበት፣ሳይንስና ሃይማኖት ተደጋግፈው የሚኖሩበት ነው። በእስላማዊ ስልጣኔ ዘንድ ያለው ውስጣዊ ሰላምና መረጋጋት ከላይ የተጠቀሱትን ሁሉ በተመቻቸና ቀለል ባለ ሁኔታ በአማኙ አእምሮ ውስጥ አካቶ ከሚይዘው ተውሒድ የሚመነጭና በጉልህ የሚታይ አንዱ መገለጫው ነው። በእስላም ውስጥ ይህ ዓለማዊ ሕይወት በራሱ ግብ ወይም ዓላማ ሳይሆን ለመጭው ዘላለማዊ የኣኽራ ሕይወት የሚያገለግል ስንቅ የሚዘራበት ማሳና ወደዚያ የሚያሸጋግር መተላለፊያ ብቻ ነው። ይህም ከሚከተለው የአላህ (ሱ.ወ.) ቃል

አእምሮና ሎጂክ

‹‹ከእስላም ድንቅ ባሕርያት አንዱ በአእምሮ ላይ የሚመረኮዝ መሆኑ ነው። ተከታዮቹን ይህን ሕያው መለኮታዊ በረከት ውድቅ እንዲያደርጉ ፈጽሞ አይጠይቃቸውም። እስላም እንደዚሁ መፈተሽና መጠየቅን አፍቃሪ ነው። ከማመናቸው በፊት እንዲያጠኑ እንዲመረምሩና እንዲያስተውሉ ለተከታዮቹ ጥሪ ያደርጋል።እስላም ‹ማንኛውንም ነገር ትክክለኛ ስለመሆኑ ማስረጃ አቅርብበትና በጎ የሆነውን ያዝ› የሚለውን ጥበባዊ ብሂል ይደግፋል። ጥበብ በተገኘበት ሁሉ ተገቢ ባለቤቱ እርሱ የሆነ የአማኙ የጠፋ ዕቃ በመሆኑ ይህ ለእስላም እንግዳ ነገር አይደለም። እስላም የአእምሮና የሎጂክ ሃይማኖት ነው። ለዚህም ነው በመሐመድ ላይ የወረደው (የተገለጠው) የመጀመሪያው ቃል ‹አንብብ› (እቅረእ) የሚል ቃል ሆኖ የምናገኘው። የእስላም መፈክርም ኪኢማን በፊት ማስተዋል ማስተንተን መመርመር መሆኑም ለዚህ ነው። እስላም እውነታ ነው፤መሣሪያው ዕውቀት ነው፤ደመኛ ጠላቱ ማይምነት ነው።››

ሃሩን ሊዮን

XXXXXXXXXX

ድንቅ የሆነ ብልህ መፍትሔ

‹‹ቁርኣን ለዘመናችን ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ሞራላዊ ችግሮች ድንቅ የሆነ ብልህ መፍትሔ ያስቀምጣል። ሙሐመድ አላህ እንዲያደርስ ያዘዘውን መልክት በማድረስ ስኬታማ ከመሆኑ አኳያ የቁርኣንን ጥበብ መጠራጠር የሚቻል አይደለም። በኔ እምነት ሃይማኖታዊ አቋማችን የፈለገውንም ቢሆን የቁርኣንን መልክት የመካው ሁኔታ ድንቅ ቅርንጫፍ አድርገን መውሰድ ይኖርብናል።››

ሞንት ጎመሬ ዋት

እንግሊዛዊ ኦሪየንታሊስት



በግልጽ የምንረዳው ነው፦

{وَٱبۡتَغِ فِيمَآ ءَاتَىٰكَ ٱللَّهُ ٱلدَّارَ ٱلۡأٓخِرَةَۖ وَلَا تَنسَ نَصِيبَكَ مِنَ ٱلدُّنۡيَاۖ وَأَحۡسِن كَمَآ أَحۡسَنَ ٱللَّهُ إِلَيۡكَۖ وَلَا تَبۡغِ ٱلۡفَسَادَ فِي ٱلۡأَرۡضِۖ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ ٱلۡمُفۡسِدِينَ ٧٧} [القصص: ٧٧]،

‹‹አላህም በሰጠህ ሀብት የመጨረሻይቱን አገር ፈልግ፤ከቅርቢቱም ዓለም ፋንታህን አትርሳ፤አላህም ወደ አንተ መልካምን እንዳደረገልህ (ለሰዎች) መልካምን አድርግ፤በምድርም ውስጥ ማጥፋትን አትፈልግ፤አላህ አጥፊዎችን አይወድምና፤(አሉት)፡፡›› [አል ቀሶስ:77],

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَإِذَا قُضِيَتِ ٱلصَّلَوٰةُ فَٱنتَشِرُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَٱبۡتَغُواْ مِن فَضۡلِ ٱللَّهِ وَٱذۡكُرُواْ ٱللَّهَ كَثِيرٗا لَّعَلَّكُمۡ تُفۡلِحُونَ ١٠} [الجمعة: 10]؛

‹‹ሶላቲቱም በተፈጸመች ጊዜ፤በምድር ላይ ተበተኑ፤ከአላህም ችሮታ ፈልጉ፤አላህንም በብዙ አውሱ፤ልትድኑ ይከጀላልና፡፡››[አል ጁሙዓህ:10]

ጥሩ ሕይወት

‹‹እስላምን በሚመለከት ፍትሐዊ መሆን ከፈለግን፣በትምሕርቶቹ ውስጥ ወደ በጎ ነገር የሚያነጣጥር ብርቱ የሆነ ወሳኝ ኃይል እንደሚገኝ፣በዚህ ኃይል ትምሕርቶች መሰረት የሚመራ ሕይወትም ከስነምግባር አኳያ ምንም ጉድፍ የሌለበት መልካም ሕይወት መሆን እንደሚችል መስማማት ይኖርብናል። እነዚህ ትምሕርቶች ለአላህ ፍጥረታት በሙሉ ርህሩህ መሆንን፣በሰዎች የርስ በርስ ግንኙነቶች ውስጥ ታማኝነትን፣ፍቅርንና ፍጹምነትን፣የራስ ወዳድነትን ስሜት መርታትንና የተቀሩትንም ምግባረ ሰናይ ተግባራት ይጠይቃሉ። የዚህ ሁሉ ድምር ውጤትም ትጉህ አማኝ የሆነ አንድ ሙስሊም፣ስነምግባር ከሚፈልገው ምርጥ አነዋነዋር ጋር የተጣጣመ ሕይወት ይናራል ማለት ይሆናል፡፡››

ጎልድ ተሲሀር
ይሁዲ ኦሪየንታሊስት

ይህም ሶላቱን ሰግደህ ካበቃህ በኋላ ሐላል ወደሆነው ዓለማዊ ሥራህ ተሰማራ፤ለአላህ ፍጹምነትን ሰንቀህና የርሱን ምንዳና ሽልማት እያሰብክ ተግተህ ሥራ ማለት ነው። ነቢዩም ﷺ ከባልደረቦቻቸው ለአንዱ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹የአላህን ምንዳና ውዴታውን እያሰብክ በምታወጣው ወጭ ለሚስትህ ቀለብ በምታውለው ነገር እንኳ ቢሆን ምንዳ ታገኝበታለህ፡፡››[በማሊክ የተዘገበ] ይህም ማለት አንድ ሙስሊም ግዴታ የሆነበትን የቤቱን ወጭ ሲያወጣ እንኳ፣አላህን እያሰበ እስካደረገው ድረስ ልክ እንደ መደበኛው ዕባዳ ሁሉ ከአላህ (ሱ.ወ.) አጅር ያገኝበታል ማለት ነው። እናም በኛ ሃይማኖት ውስጥ በዱንያ ተውጠን ኣኼራን ካለመዘንጋት ግዴታ ጋር ዱንያን ከኣኼራ የሚነጥል ነገር የለም። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تُلۡهِكُمۡ أَمۡوَٰلُكُمۡ وَلَآ أَوۡلَٰدُكُمۡ عَن ذِكۡرِ ٱللَّهِۚ وَمَن يَفۡعَلۡ ذَٰلِكَ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡخَٰسِرُونَ ٩} [المنافقون: ٩]،

‹‹እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ገንዘቦቻችሁና ልጆቻችሁ አላህን ከማስታወስ አያታሉዋችሁ፤ይህንንም የሚሠሩ ሰዎች፣እነዚያ እነሱ ከሳሪዎቹ ናቸው፡፡››[አል ሙናፊቁን:9]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَٱبۡتَغِ فِيمَآ ءَاتَىٰكَ ٱللَّهُ ٱلدَّارَ ٱلۡأٓخِرَةَۖ وَلَا تَنسَ نَصِيبَكَ مِنَ ٱلدُّنۡيَاۖ وَأَحۡسِن كَمَآ أَحۡسَنَ ٱللَّهُ إِلَيۡكَ} [القصص: ٧٧]،

‹‹አላህም በሰጠህ ሀብት የመጨረሻይቱን አገር ፈልግ፤ከቅርቢቱም ዓለም ፋንታህን አትርሳ፤አላህም ወደ አንተ መልካምን እንዳደረገልህ (ለሰዎች) መልካምን አድርግ፤በምድርም ውስጥ ማጥፋትን አትፈልግ፤አላህ አጥፊዎችን አይወድምና፤(አሉት)፡፡›› [አል ቀሶስ:77]

ሥራን ማፍቀር፣ሚስትን ማፍቀር፣ልጆችና ቤተሰብን ማፍቀርና መንከባከብ . . በሸሪዓው ገደብ ውስጥ፣በነቢዩ ﷺ ፈለግና አላህን በማሰብ እስከሆነ ድረስ የሃይማኖቱ አካል ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلۡ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحۡيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٦٢} [الأنعام: ١٦٢]،

‹‹ስግደቴ፣መገዛቴም፣ሕይወቴም፣ሞቴም፣ለዓለማት ጌታ ነው በል፡፡››[አል አንዓም:162]

ሕይወታችን በጥቅሉ የአላህ ነው፡፡ የነፍስና የሥጋዊ ፍላጎት ጉዳይ የሆነው ክፍልም ጭምር፣ከቅርብና ከሩቅ ሰዎች ጋር፣ከደጋፊና ከተቃዋሚም ጋር፣ያለው ውጫዊ ሰላምም እንዲሁ ቅን ልቦናና መልካም ኒያ እስካለ ድረስ ለአላህ ትእዛዛት የመገዛት (የጧዓ) መገለጫ ነው፡፡ አንድ ሙስሊም ሌላ ሙስሊም ወንድሙን ሲያገኝ የሚያቀርብለት የመጀመሪያው ሰላምታም ‹‹አስሳሙ ዐለይኩም ወረሕመቱሏህ ወበረካቱህ›› የሚል ሲሆን ‹‹የአላህ ሰላም፣እዘነቱና በረከቶቹ ባንተ ላይ ሁን›› ማለት ነው፡፡ ሁሉም ሃይማኖቶች በእስላማዊው ሥርዓት ውስጥ በደስተኛነትና በተደረገላቸው ጥበቃ ረክተው እንደ ኖሩት ዓይነት በየትኛውም ሌላ ሥርዓት ውስጥ ረክተው ኖረው አያውቅም፡፡ ሙስሊሞች

የተሟላ ክቡር ሰብእና ያላቸው ሰዎች

‹‹ሙስሊሞች - በጥቆማ እንደሚባለሁ ሁሉ - ከክርስቲያኖች ይበልጥ የተሟላ ክቡር ሰብእና ነበራቸው፡፡ ከነርሱ ይበልጥ ቃል ኪዳን ጠባቂዎች፣ከነርሱም ይበልጥ ለተሸናፊዎች ርህሩሆች ነበሩ፤ክርስቲያኖች በ1099 ዓመተ ልደት ኢየሩሳሌምን ሲይዙ የፈጸሙትን ዓይነት አረመኔያዊ ተግባር ሙስሊሞች በታሪካቸው ውስጥ ፈጽመውት አያውቁም ማለት ይቻላል፡፡››

ዎል ዲዮራንት
አሜሪካዊ ደራሲ

https://www.path-2-happiness.com/am

የመንፈስ እርካታ

ዴል ካርኔጂ

አሜሪካዊ ደራሲ

የእስላም ታላቅነት



ነስሪ ሰልሀብ

ሊባኖሳዊ ስነጽሑፍ ሰው

በከፊል ወደ ኋላ በማሽቆልቆላቸው ግን ዓለማችን ብዙ ነገር አጥታለች። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَا يَجۡرِمَنَّكُمۡ شَنَـَٔانُ قَوۡمٍ أَن صَدُّوكُمۡ عَنِ ٱلۡمَسۡجِدِ ٱلۡحَرَامِ أَن تَعۡتَدُواْۘ وَتَعَاوَنُواْ عَلَى ٱلۡبِرِّ وَٱلتَّقۡوَىٰۖ وَلَا تَعَاوَنُواْ عَلَى ٱلۡإِثۡمِ وَٱلۡعُدۡوَٰنِۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۖ إِنَّ ٱللَّهَ شَدِيدُ ٱلۡعِقَابِ ۝٢} [المائدة: ٢].

‹‹ከተከበረው መስጊድ ስለከለከሉዋችሁ ሰዎችን መጥላትም (በነሱ ላይ) ወሰን እንድታልፉ አይገፋፋችሁ፤በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ፤ግን በኃጢአትና ወሰንን በማለፍ አትረዳዱ። አላህንም ፍሩ፤አላህ ቅጣተ ብርቱ ነውና።››[አል ማእዳህ:2]

7- የጥራትና የፍቅር ስልጣኔ፦

እስላማዊው ሸሪዓ ግለሰብ አባላቱ የንጹሕ ልብ፣የቅን ልቦናና የጸዳ ሕሊና ባለቤቶች እንዲሆኑ ግዴታ ይጥልባቸዋል። አላህ (ሱ.ወ.) የምእመናንን ዱዓእ አስመልክቶ እንዲህ ብሏል፦

{وَٱلَّذِينَ جَآءُو مِنۢ بَعۡدِهِمۡ يَقُولُونَ رَبَّنَا ٱغۡفِرۡ لَنَا وَلِإِخۡوَٰنِنَا ٱلَّذِينَ سَبَقُونَا بِٱلۡإِيمَٰنِ وَلَا تَجۡعَلۡ فِي قُلُوبِنَا غِلّٗا لِّلَّذِينَ ءَامَنُواْ رَبَّنَآ إِنَّكَ رَءُوفٞ رَّحِيمٌ ۝١٠} [الحشر: ١٠]،

‹‹እነዚያም ከበኋላቸው የመጡት፣ጌታችን ሆይ! ለኛም ለነዚያም በእምነት ለቀደሙን ወንድሞቻችን ምሕረት አድርግ። በልቦቻችንም ውስጥ ለነዚያ ለአመኑት (ሰዎች) ጥላቻን አታድርግ። ጌታችን ሆይ! አንተ ርኅሩህ አዛኝ ነህና ይላሉ።››[አል ሐሽር:10]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَوۡمَ لَا يَنفَعُ مَالٞ وَلَا بَنُونَ ۝٨٨ إِلَّا مَنۡ أَتَى ٱللَّهَ بِقَلۡبٖ سَلِيمٖ ۝٨٩} [الشعراء: ٨٨- ٨٩]،

‹‹ገንዘብም ልጆችም በማይጠቅሙበት ቀን፤ወደ አላህ በንጹህ ልብ የመጣ ሰው ቢኾን እንጅ።››[አል ሹዐራ:88-89]

ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹እርስ በርስ አትጠላሉ፣አትመቀኛኙ፣አትዶላለቱ፣ወንድማማች የአላህ ባሮች ሁኑ እንጅ። አንድ ሙስሊም ወንድሙን ከሦስት ቀናት በላይ በማኩረፍ ሲገናኙ ይህኛው ፊቱን ማዞር፣ያኛውም ፊቱን ማዞር አይፈቀድም፤በላጫቸው አስቀድሞ ሰላምታ ሚያቀርበው ነው።››[በሙስሊም የተዘገበ] መዋደድንና ተግባቢ መሆንን ሲያበረታቱም ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ነፍሴ በእጁ በሆነች (አላህ) እምላለሁ፣እስክታምኑ ድረስ ጀነት አትገቡም፤እስክትዋደዱ ድረስም አታምኑም፤ይህንን የሚያጸና ነገር ልንገራችሁን? በመካከላችሁ ሰላምታን አጉልታችሁ አቅርቡ (ሰላምታን ለሁሉም አዳርሱ)።››[በእብን ማጀህ የተዘገበ] የአላህ መልክተኛ ከሰዎች በላጩ ማነው? ተብለው ሲጠየቁ ፦ ‹‹ልቡ ከክፋት የጸዳ (መኽሙሙል ቀልብ)፣አንደበቱ በጣም እውነተኛ የሆነ ሰው ሁሉ ነው።›› አሉ፤‹‹አንደበቱ በጣም እውነተኛ የሆነ›› ማለት ምን እንደሆነ እናውቃለን፣‹‹ልቡ ከክፋት የጸዳ (መኽሙሙል ቀልብ) ማለት ምን ማለት ነው? ብለው ጠየቋቸው፤እሳቸውም፦ ‹‹አላህን የሚፈራ፣ጽዱ፣ኃጢአት፣ግፍ፣ቋጠሮም ሆነ ምቀኝነት የሌለበት ልብ ነው።›› ብለው መለሱ።

ጉድለቱ ከኛ ነው

‹‹ለዛሬው የማሽቆልቆል ሁኔታ ምክንያት የሆነው የሙስሊሞች ቸልተኝነት እንጂ የእስላማዊ ትምህርቶች ጉድለት አለመሆኑ ግልጽ ሊሆንልን ይገባል።››

ዮፖልድ ፋይስ

ኦስትራዊ ፈላስፋ

8- መንፈሳዊ ሥጋዊ ስልጣኔ፦

እስላማዊው ስልጣኔ የመንፈስ ፍካትን ይዞ የመጣ ሲሆን፣በተመሳሳይም የሰውን ሥጋዊና ቁሳዊ ጎንም አልዘነጋም። አላህ (ሱ.ወ.) ሰውን ከሥጋና ከነፍስ ፈጥሮት በሁሉም ቁሳዊና መንፈሳዊ የሕይወት ገጽታዎች የሚያስፈልጉትን ሁሉ አስታጥቆታል። ለሥጋዊ አካሉ በምድር ላይ የሚኖርበትን ምቹ አካባቢን ሲያሰናዳለት፣ለመንፈሳዊ ጎኑ ደግሞ በመልክተኞቹ አማካይነት የተላከለትን የመለኮታዊ ወሕይ (ራእይ) ቀለብ አመቻችቶለታል። አላህ (ሱ.ወ.) የሰውን መንፈሳዊ ጎን አፈጣጠር በማስመልከት እንዲህ ብሏል፦

https://www.path-2-happiness.com/am

{وَإِذۡ قَالَ رَبُّكَ لِلۡمَلَٰٓئِكَةِ إِنِّي خَٰلِقُۢ بَشَرٗا مِّن صَلۡصَٰلٖ مِّنۡ حَمَإٖ مَّسۡنُونٖ ﴿٢٨﴾ فَإِذَا سَوَّيۡتُهُۥ وَنَفَخۡتُ فِيهِ مِن رُّوحِي فَقَعُواْ لَهُۥ سَٰجِدِينَ ﴿٢٩﴾} [الحجر: ٢٨- ٢٩]؛

‹‹ጌታህም ለመላእክት ባለ ጊዜ፣(አስታውስ) ፦ እኔ ሰውን ከሚቅጨለጨል ሸክላ፣ከሚገማ ጭቃ እፈጥራለሁ። ፍጥረቱን ባስተካከልኩትና ከመንፈሴ በነፋሁበትም (ነፍስ በዘራሁበት) ጊዜ፣ለርሱ ሰጋጆች ኾናችሁ ውደቁ።››[አል ሒጅር:28-29]

ነፍስና ሥጋ፣መንፈስና አካል አንዱ ከሌላው በሞት ብቻ እንጂ የማይነጠል የተቃቀፉ ነገሮች ናቸው። እያንዳንዳቸውም የራሱ የሆኑ ፍላጎቶችና ጥያቄዎች አሉት። አካል በምግብ በመጠጥና በልብስ የሚኖር ሲሆን፣በአንዱ ጎን ብቻ ብንወሰን ግን ጉዳቱን በሁለቱም ጎኖች ላይ ሲንፀባረቅ እናያለን። የሰው ልጅ በመብላት ብቻ ቢወሰን የተረጋጋ መልካም ሕይወት መምራት የማይችል ደካማና ቀአቅመ ቢስ ሆኖ እናገኛዋለን፤በመጠጥና በልብስ ብቻ ቢወሰንም እንዲሁ።

ከአካል ፍላጎቶች ውስጥ አንዱን ማጓደል በሁለቱም ጎኖቹ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ሲሆን፣ለራሱ መኖር የሚከብደው ከመሆኑም ባሻገር ሌላኛው ጎኑን የተረጋጋ ሕይወት ይኖር ዘንድ መርዳት ይሳነዋል። መንፈስም እንዲሁ የራሱ ፍላጎቶች ሲኖሩት፣ነፍስ ያለ ፍቅር፣ያለ አበርክቶም ሆነ ያለ መስዋእትነት አትኖርም።

9- ለሰብአዊ ፍጡርና ለሰብአዊ መብቱ ትኩረት የሚሰጥ ስልጣኔ ፦

ሰብአዊ መብቶችን መተግበር አንድ አገር የፍትህና የእኩልነት መርሆዎችን ምን ያህል እንደሚያከብር፣የዜጎቹን መብቶችና ነጻነቶች ምን ያህል እንደሚጠብቅ ጠቋሚ መስፈርት መሆኑ በሁሉም ዘንድ ይታወቃል። ያ ሕዝብ መብቶቹን በማስከበር በኩል ያለውን ግንዛቤና የንቃተ ሕሊና ደረጃ የሚያመለክት መለኪያም ነው። የዴሞክራሲያዊ ሥርዓቶች ዋነኛው የማእዘን ድንጋይም ሰብአዊ መብቶችን ማክበር ነው።

እስላማዊው ስልጣኔ ሰብአዊ መብቶችን በማስከበር ረገድ በተጨባጭ መሬት ወርዶ በተግባር የታየ ልዩ የሆነ ተምሳሌታዊ ድል አስመዝግቧል። በዚህም ሰብአዊ መብት ባዶ መፈክር ብቻ አለመሆኑን በተግባር በማሰየት እስላማዊው ስልጣኔ ታላቅነቱን አስመስክሯል። በመሆኑም እሰላም ዘንድ ሰብአዊ መብቶችን ልዩ የሚያደርጉ አበይት ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው ፦

1- የነዚህ መብቶች ምንጭ ሉዓላዊነትና የሕግ አውጭነት ስልጣን የአላህ (ሱ.ወ.) ብቻ መሆኑን በሚያረጋግጠው መርህ ላይ የተመሰረተ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنِ ٱلۡحُكۡمُ إِلَّا لِلَّهِۖ يَقُصُّ ٱلۡحَقَّۖ وَهُوَ خَيۡرُ ٱلۡفَٰصِلِينَ ﴿٥٧﴾} [الأنعام: ٥٧]؛

‹‹ፍርዱ ለአላህ ብቻ ነው፤እውነትን ይፈርዳል፤እርሱም ከፈራጆች ሁሉ በላጭ ነው በላቸው።››[አል አንዓም:57]

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

እስላማዊው የሰብአዊ መብቶች ፕሮጄክት ጉዳዩን የሚመለከተው፣መለኮታዊው እይታ ይህን ሰብአዊ ፍጡርና የሚበጀውን ነገር በሚመለከትበት እይታ መሆኑ::

2- ጽናቱና በዘመን መለዋወጥም ሆነ በሁኔታዎች መቀያየር የማይለወጥ መሆኑ::

3- መብቶቹ የሚነሱት ከስምረት (እሕሳን) ደረጃ መሆኑን ትኩረት ውስጥ ማስገባት፡- እስላም ውስጥ መብቶች አንድ የአላህ አገልጋይ አላህን በመፍራትና ትእዛዛቱን በመፈጸም ረገድ የሚይዘውን የስምረት ደረጃ የሚከተሉ ናቸው:: ይህ የእሕሳን ደረጃ በሚከተለው የነቢዩ ﷺ ቃል የተነገረው ነው ፦ ‹‹አላህን ልክ በዓይን እንደምታየው ሆነ እርሱን መግገዛት ነው፣አንተ ባታየውም እርሱ ያየሃልና::››[በሙስሊም የተዘገበ]

4- በሰብአዊ መብቶችና በዚህ ሃይማኖት ተፈጥሮ መካከል የተሟላ መጣጣም መኖሩ ፦ እስላም ሰብአዊ መብቶችን እንዲሁ ባዶ ቃላት አድርጎ አልተዋቸውም፤በሸሪዓዊ ሕግጋት ማእቀፍ ውስጥ በማስቀመጥ ከሸሪዓዊ ዓላማዎች አኳያ ተመልክቶ ከስነምግባራቱና ከግብረገብነት እሴቶቹ ጋር ያጣምራቸዋል:: እነዚያን ስነምግባራት ማጓደልን ሰብአዊ መብቶቹን ማጓደል አድርጎ ይመለከታል:: በመጨረሻም ከሃይማኖት ጋር በማስተሳሰር ምንጫቸውን መለኮታዊ ምንጭ ያደርጋል:: ስለዚህም ሰብአዊ መብቶች መብቶች ብቻ ሳይሆኑ ከአንድ ሙስሊም ሃማኖታዊ ግዴታዎች አንዱ ሆነው ይቆጠራሉ:: በመሆኑም እስላም ውስጥ ያለው ሰብአዊ መብቶች መዋቅር ከሃይማኖቱ መለኮታዊ ባህሪ ጋር በተጣጣመ መልኩ የተሟላ መዋቅር ነው::

5- እስላም ውስጥ ባለው የሰብአዊ መብቶች መንደርደሪያ፣የማህበረሰብ ልዕልና የግለሰቦች ልዕልና ቅርንጫፍ እንጂ በሰው ሠራሽ ሥርዓቶች ውስጥ እንደሚስተዋለው የዚህ ተቃራኒ አይደለም:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

ወናው ዓለም

መርመዱክ ፒክትሆል
እንግሊዛዊ ጸሐፊ

{مِنْ أَجْلِ ذَٰلِكَ كَتَبْنَا عَلَىٰ بَنِيٓ إِسْرَٰٓءِيلَ أَنَّهُۥ مَن قَتَلَ نَفْسًۢا بِغَيْرِ نَفْسٍ أَوْ فَسَادٍ فِي ٱلْأَرْضِ فَكَأَنَّمَا قَتَلَ ٱلنَّاسَ جَمِيعًا وَمَنْ أَحْيَاهَا فَكَأَنَّمَآ أَحْيَا ٱلنَّاسَ جَمِيعًا وَلَقَدْ جَآءَتْهُمْ رُسُلُنَا بِٱلْبَيِّنَٰتِ ثُمَّ إِنَّ كَثِيرًا مِّنْهُم بَعْدَ ذَٰلِكَ فِي ٱلْأَرْضِ لَمُسْرِفُونَ ۝٣٢} [المائدة: ٣٢].

‹‹በዚህ ምክንያት በእስራኤል ልጆች ላይ፣እነሆ ያለ ነፍስ (መግደል)፣ወይም በምድር ላይ ያለማጥፋት፣ነፍስን የገደለ ሰው፣ሰዎቹን ሁሉ እንደ ገደለ ነው፤ሕያው ያደረጋትም ሰው፣ሰዎቹን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው፣ማለትን ጻፍን፤መልክተኞቻችንም በግልጽ ተአምራት በእርግጥ መጡዋቸው፤ከዚያም፣ከዚህ በኋላ ከነሱ ብዙዎቹ በምድር ላይ ወሰንን አላፊዎች ናቸው::››[አል ማእዳህ:32]

6- ሰብአዊ መብቶች በእስላም ውስጥ ከዘመን አኳያ ከሁሉም ቀዳሚ ነው:: እስላም ለሰው ልጆች እነዚህን መብቶች ያረጋገጠው፣ዛሬ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓቶች ውስጥ እንዳሉት የሰብአዊ መብቶች አመጣጥ መነሻና ታሪክ ዓይነት፣በፈረንሳይ በአሜሪካና በሌሎችም አገሮች እንደሆነው ከዘመናት የአመለካከት ግጭቶች፣ከመራራ ትግሎችና አብዮቶች በኋላ የተገኙ አይደሉም:: የሰብአዊ መብት መርሆዎችና ድንጋጌዎች ጸንተው የመጡት ጉዳዩ ሳይነሳ፣ጥያቄ ሳይቀርብበትና ትግልም ሳይካሄድ ከአላህ (ሱ.ወ.) በተላለፈ መለኮታዊ ወሕይ ተረጋግጠው ነው::

7- በሌሎች ሥርዓቶች ውስጥ እንዳለው ዓይነት ፍልስፍናዊ ቅብ የተቀቡ ሳይሆን፣ተጨባጭና ከተግባራዊ ሕይወት ጋር የተሳሰሩ፣በሰው ልጅ እውነተኛ ፍላጎት ላይ ያነጣጠሩ ናቸው::

8- ሰብአዊ መብትን በተመለከተ እስላማዊ ሸሪዓ ልዩ የሆነባቸው ጉዳዮች ሲኖሩት ከነዚህ መካከል፦ ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች በልጆች ላይ የሚኖራቸው መብት፣የቤተ ዘመዶች መብት፣በማሕጸን የሚገኝ ጽንስ መብት፣ሃይማኖታዊና ዓለማዊ ትምህርት የመማርና የማስተማር ግለሰባዊ መብት፣በሕጋዊ መንገድ ሀብት የማፍራትና አራጣን የመከልከል መብት፣ወደ በጎ ነገር ሁሉ ጥሪ የማድረግና የማዘዝ፣ከእኩይና ክፉ ነገሮችም የመከልከል የደዕዋ መብት ይገኛሉ::

9- የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ እስላማዊ አቀራረብ በመሰረቱ በሰው ልጅ ክቡርነትና በአላህ (ሱ.ወ.) የማመንን ስሜት በማነሳሳት፣ከተሟላ የተቀናጀ የአነዋነዋር ሥርዓት ጋር በተጣጣመ መልኩ አላህ (ሱ.ወ.) በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ያለውን ሁሉ ለሰው ልጅ የገራ በመሆኑ ጽንሰ ሐሳብ ላይ የሚሞረኮዝ ነው:: የሰው ልጅ ታሪክ በየትኛውም ዘመን ሰብአዊ መብቶች ከጥቅሞች ታሳቢነት በራቀ ሁኔታ ተግባራዊ የሆኑበትን ጊዜ አይቶ አያውቅም:: ባዶ መፈክሮችን ማስተጋባት ቀላል ሲሆን ከነዚህ ባዶ ጨኸቶች በስተጀርባ ያለውን ዓለማና ፍላጎት ስንመረምር ግን እውነተኛ ዓለማቸው ሰብአዊ መብት ሳይሆን የተለየ ሌላ ነገር ሆኖ እናገኛለን::

https://www.path-2-happiness.com/am

በሙሐመድ ﷺ መላክ የተሟላ ሰውኛ ስልጣኔ ለሰው ልጆች የመጣ ሆኖ ሳለ ሙስሊሞች የኋሊዮሽ የተመለሱበትና እስላማዊው ስልጣኔ በእጃቸው እያለ ዛሬ ባሉበት ሁኔታ ላይ የሆኑበት ምክንያት ምንድነው?! የሚል ጥያቄ በአንዳንዶች ይነሳ ይሆናል። ዛሬ ሙስሊሞች ያሉበት ሁኔታ የሃይማኖታቸውን እውነታ የማይወክል መሆኑን ስንረዳ ግን አግራሞቱ ይወገዳል። ብዙዎቹ ሙስሊሞች የሃይማኖታቸውን መርሆዎች፣በሕያው መጽሐፋቸውና በነቢያቸው ﷺ ሱንና ውስጥ የተካተተውን ሁሉ ወደ ጎን በመተዋቸው የኋላ ቀርነት ሰለባ ለመሆን ተጋልጠዋል። ለእስላማዊ መርሆዎቻቸው ተገዥና ታማኝ ቢሆኑ ኖሮማ ከእስላማዊው ስልጣኔ ይበልጥ ለመላው የሰው ዘር ደስተኝነትንና መታደልን ይዞ የመጣ አንድም ስልጣኔ በታሪክ ታይቶ አያውቅም። ይህን ለማረጋገጥና በሙስሊሞች ሁኔታ ማሽቆልቆል ዓለም ያጣውን ታላቅ ትሩፋት ለማወቅ፣ታሪክን ማንበብና ሙስሊም ያልሆኑ አስተዋይና ሚዘናዊ እውቅ ግለሰቦች ሳይቀሩ የሚናገሩትን ማዳመጡ ብቻ በቂ ነው።

.የቁርኣንና የሱንና ታአምራት

እያንዳንዱ ነቢይና መልክተኛ ከአላህ አላህ (ሱ.ወ.) ለመላኩ አስረጅ የሚሆን ተአምር ይሰጠዋል። ለምሳሌ ያህል የሙሳ عليه السلام ተአምር በትራቸው ነበር። የዒሳ عليه السلام ተአምር ደግሞ ዕውርም ኾኖ የተወለደንና ለምጻምን መፈወስ፣በአላህ ፈቃድም ሙታንን ከመቃብራቸው ማስነሳት ነበር። የነቢያት መደምደሚያና የመልክተኞች መቋጫ የሆኑት የሙሐመድ ﷺ ታአምር ደግሞ መልክታቸው እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚቆይና ለሁሉም ዘመንና ስፍራ ምቹ የተደረገ ከመሆኑ ጋር በተጣጣመ መልኩ ዘላለማዊ ሕያው መጽሐፍ የሆነው ታላቁ ቁርኣን ነው። ቁርኣን የሕይወት መመሪያ መጽሐፍ ከሆነ ዘንዳ፣ይህ መጽሐፍ በሁሉም ነገሩ ተአምራዊ ነው። የዚህ ቁርኣን ታምራዊነትና አሸናፊነት ለነቢዩ ﷺ መልክት እውነተኛነትና ለነቢዩ ፍጹም ሐቀኝነት ዛሬም አስረጅ ተአምር ሆኖ ቀጥሏል። ሲሳይ ሰጭ፣ሕያውና ከሁሉም የተብቃቃ ከሆነው ፈጣሪ በነቢያት መደምደሚ አማካይነት የተላለፈ፣ለሁሉም ዘመንና ቦታ ምቹና ተስማሚ የሆነ መጽሐፍ ነው። ቀደም ሲል ከተገለጹት የተአምራዊነት ገጽታዎቹ በተጨማሪ፣ከዘመናችን ተመራማሪ ሳይንቲስቶች ጥረት መረዳት እንደ ተቻለው፣ቁርኣን እግረ መንገዱን በሚያነሳቸው ሳይንሳዊ ጉዳዮች ላይም ተአምራዊ ነው። ሳይንቲስቶች ባደረጉት ጥናት እንደ ደረሱበት ቅዱስ ቁርኣን በቅርቡ እንጂ ዘመናዊው ሳይንስ ያልደረሰባቸውን ብዙ ሳይንሳዊ እውነታዎችን ያከተተ መሆኑ ተረጋግጧል። ከነዚህም መካከል ለአብነት ያህል፦ የሰው ልጅ ጽንስ ዕድገት ደረጃዎችን ሰዎች ስለዚህ ጉዳይ ምንም ነገር ከማያውቁበት ከበርካታ ምእተ ዓመታት በፊት በተራቀቀ ሁኔታ መግለጹ አንዱ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) ይህን በማስመልከት እንዲህ ብሏል፦

{وَلَقَدْ خَلَقْنَا ٱلْإِنسَٰنَ مِن سُلَٰلَةٍ مِّن طِينٍ ﴿١٢﴾ ثُمَّ جَعَلْنَٰهُ نُطْفَةً فِى قَرَارٍ مَّكِينٍ ﴿١٣﴾ ثُمَّ خَلَقْنَا ٱلنُّطْفَةَ عَلَقَةً فَخَلَقْنَا ٱلْعَلَقَةَ مُضْغَةً فَخَلَقْنَا ٱلْمُضْغَةَ عِظَٰمًا فَكَسَوْنَا ٱلْعِظَٰمَ لَحْمًا ثُمَّ أَنشَأْنَٰهُ خَلْقًا ءَاخَرَ فَتَبَارَكَ ٱللَّهُ أَحْسَنُ ٱلْخَٰلِقِينَ ﴿١٤﴾} [المؤمنون: ١٢ـ ١٤]،

‹‹በእርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው። ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ፣የፍትወት ጠብታ አደረግነው። ከዚያም ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርን፤የረጋውንም ደም ቁራጭ ሥጋ አድርገን ፈጠርን፤ቁራጭዋንም ሥጋ አጥንቶች አድርገን ፈጠርን፤አጥንቶቹንም ሥጋን አለበስናቸው፤ከዚያም (ነፍስን በመዝራት) ሌላ ፍጥረትን አድርገን አስገኘነው፤ከሰዓሊዎችም ሁሉ በላጭ የኾነው አላህ ላቀ።››[አል ሙእምኑን፡12-14]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَخْلُقُكُمْ فِى بُطُونِ أُمَّهَٰتِكُمْ خَلْقًا مِّنۢ بَعْدِ خَلْقٍ فِى ظُلُمَٰتٍ ثَلَٰثٍ ذَٰلِكُمُ ٱللَّهُ رَبُّكُمْ لَهُ ٱلْمُلْكُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ فَأَنَّىٰ تُصْرَفُونَ ﴿٦﴾} [الزمر: ٦]،

‹‹በእናቶቻችሁ ሆዶች ውስጥ፣በሦስት ጨለማዎች ውስጥ (በሆድ በማሕጸንና በእንግዴ ልጅ) ከመፍጠር በኋላ፣(ሙሉ) መፍጠርን ይፈጥራችኋል፤ይሃችሁ ጌታችሁ አላህ ነው። ሥልጣኑ የርሱ ብቻ ነው፤ከርሱ ሌላ አምላክ የለም፤ታዲያ ወዴት ትዞራላችሁ?››[አል ዙመር፡6]

ሳይንቲስቶችና ሐኪሞች ይህንን ከራሳቸው ግኝቶችና ማመሳከሪያ ዋቢዎች ጋር አነጻጽረው ሲያጠኑ ሙሉ በሙሉ ውስጠ ዐዋቂው አላህ (ሱ.ወ.) እንዳለው ሆኖ ነበር ያገኙት። በተጨማሪም የመዳሰስ ስሜት መነሻ ስፍራን በተመለከተ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَا سَوْفَ نُصْلِيهِمْ نَارًا كُلَّمَا نَضِجَتْ جُلُودُهُم بَدَّلْنَٰهُمْ جُلُودًا غَيْرَهَا لِيَذُوقُوا۟ ٱلْعَذَابَ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَزِيزًا حَكِيمًا ﴿٥٦﴾} [النساء: ٥٦]،

‹‹እነዚያን በታምራታችን የካዱትን በእርግጥ እሳትን እናገባቸዋለን፤ስቃይን እንዲቀምሱ ቆዳዎቻቸው በተቃጠሉ ቁጥር ሌሎችን ቆዳዎች እንለውጥላቸዋለን፤አላህ አሸናፊ ጥበበኛ ነውና።››[አል ኒሳእ፡56]የጠፈርን መስፋፋትና እየተዘረጋጋ መሄድ

የጽንስ እድገት ደረጃዎች ገለጻ

‹‹ቁርኣን የአላህ ቃል መሆኑን አምኖ ለመቀበል ችግር የለብኝም። ቁርአን ውስጥ የቀረበው የጽንስ ገለጻ በሰባተኛው ክፍለ ዘመን በነበረው የሰው ልጅ የሳይንሳዊ ዕውቀት ደረጃ ላይ ሊመሰረት አይችልም። ሊደረስበት የሚችለው ብቸኛው ማጠቃለያ እነዚያ ገለጻዎች ከአላህ ለሙሐመድ የተገለጡ ናቸው የሚለው ብቻ ነው።››

ፕሮፌሰር ዮሽዮዲ ኮዛን
የቶኪዮ ጠፈር ምርምር ጣቢያ ዳይሬክተር

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

ሲገልጽም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَٱلسَّمَآءَ بَنَيۡنَٰهَا بِأَيۡيْدٍ وَإِنَّا لَمُوسِعُونَ ۝٤٧} [الذاريات: ٤٧]،

‹‹ሰማይንም በኃይል ገነባናት፤እኛም በእርግጥ [ለማስፋት] ቻዮች ነን፡፡››[አል ዛሪያት፡47]

ፀሐይ በራሷ ምሕዋር የምትጓዝ መሆኑን ሲገልጽ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَءَايَةٌ لَّهُمُ ٱلَّيۡلُ نَسۡلَخُ مِنۡهُ ٱلنَّهَارَ فَإِذَا هُم مُّظۡلِمُونَ ۝٣٧ وَٱلشَّمۡسُ تَجۡرِى لِمُسۡتَقَرٍّ لَّهَاۚ ذَٰلِكَ تَقۡدِيرُ ٱلۡعَزِيزِ ٱلۡعَلِيمِ ۝٣٨} [يس: ٣٧-٣٨].

‹ሌሊቱም ለነሱ ምልክት ነው፤ከርሱ ላይ ቀንን እንገፍፋለን፣ወዲያውኑም እነሱ በጨለማ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ፀሐይም ለርሷ ወደ ኾነው መርጊያ ትሮጣለች፤ይህ የአሸናፊው፣የዐዋቂው፣አምላክ ውሳኔ ነው፡፡››[ያሲን፡37]

የነቢዩ ሱንናም ከዚህ ተአምር የራቀ አይደለም፡፡ ከእመ ምእመናን ዓእሻ (ረ.ዐ.) በተላለፈው መሰረት፣የአላህ መልክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ እያንዳንዱ የኣደም ልጅ ሦስት መቶ ስልሳ የአጥንት መገጣጠሚያዎች ይዞ ነው የተፈጠረው፤በነዚያ ሦስት መቶ ስልሳ አጥንቶች ቁጥር፣‹አልሏሁ አክበር›፣አልሐምዱ ሊልላህ›፣‹ላእላሀ እልላልሏህ›፣‹ሱብሓነልሏህ› እና ‹አስተግፍሩልሏህ› ያለ ሰው፣ሰዎች ከሚሄዱበት መንገድ ላይ ድንጋይ ወይም እሾህ፣ወይም አጥንት ያስወገደ፣በበጎ ነገር ያዘዘ፣ወይም ከክፉ ነገር የከለከለ ሰው በዚያ ዕለት ራሱን ከእሳት ያረቀ ሆኖ ይውላል፡፡››[በሙስሊም የተዘገበ]

ዛሬ በሳይንስ እንደ ተረጋገጠው የሰው ልጅ እነዚህ አጥንቶችና መገጣጠሚያዎች ባይኖሩት ኖሮ፣ሕይወቱን መምራትና ኑሮን ማጣጣምም ሆነ የተጣለበትን በምድር ላይ የምትክነት ተልእኮ መወጣት ባልቻለ ነበር፡፡ ከዚህ ስንነሳም የፈጣሪን ታላቅ ጥበብና ድንቅ ውሳኔ ለሚመሰክረው ለዚህ ትልቅ ጸጋ የሰው ልጅ በየቀኑ ምስጋና የማድረስ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ በዚህ ሐዲስ ውስጥ ተአምራዊው ነገር ነቢዩ ﷺ እንዲህ ዓይነቱ ዕውቀት የትምና ማንም ዘንድ ባልነበረበት ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንዲህ በረቀቀ ሁኔታ የሰው አጥንት መገጣጠሚያዎችን መግለጻቸው ነው፡፡ እንኳ በዚያ ዘመን ዛሬ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን አብዛኛው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ብዙ የሕክምና ሳይንስ መምሕራን ጭምር ይህን አያውቅም!! ዛሬ ዘመናዊው ሳይንስ ልክ ነቢዩ ﷺ ከአስራ አራት ክፍለ ዘመናት በፊት እንደተናገሩት ባረጋገጠው መሰረት፣በሰው አካል ውስጥ ሦስት መቶ ስልሳ የአጥንት መገጣጠሚያዎች ይገኛሉ፡፡ 147ቱ በጀርባ አከርካሪ አጥንት ሲገኙ፣24ቱ በደረት፣86ቱ ከወገብ በላይ ባለው ክፍል፣88ቱ ከወገብ በታች ባለው የሰውነት ክፍል፣15ቱ ደግሞ በዳሌ ገንዳ ይገኛሉ፡፡

እዚህ ላይ የግድ መነሳት ያለበት ጥያቄ ፦ ከፈጣሪው አላህ (ሱ.ወ.) በስተቀር ይህንን የሰው ልጅ ዕውቀት በሃያኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻዎች ላይ እንጅ ያልደረሰበትን ልዩ የሆነ ሳይንሳዊና ሙያዊ እውነታ ለነቢያትና ለመልክተኞች መደምደሚያ ﷺ ማን ሊያስተምር ይችላል?! የሚለው ነው፡፡

ነቢዩን ﷺ ከሰው ግንዛቤ በላይ የሆነውን እንዲህ ያለውን ጉዳይ እንዲያነሱ ሊያደርጋቸው የሚችለውስ ማን ሊሆን ይችላል?! አላህ (ሱ.ወ.) በገደብ የለሽ ዕውቀቱ የሰው ልጅ አንድ ቀን በዚህ የአቶኖሚ ግኝት ላይ ሊደርስ እንደሚችል ስለሚውቅም ነቢዩን ﷺ አሳውቋቸዋል፡፡ ከዚህ ነቢያዊ ሐዲሥ የሚንጸባረቀው የሐቅ ብርሃን ለእኚህ የመልክተኞች መደምደሚያ ነቢይ እውነተኛነትና ከመለኮታዊ ራእይ ጋር ስላላቸው ትስስር እርግጠኝነት የጸና ማስረጃ ነው፡፡

የሳይንስና የስልጣኔ መንገድ ግን የመልካም ስነምግባር መንገድ ካልሆነ፣ለሰው ልጆች ተድላና ደስታ የማያገለግል፣ለጥፋትና ለዕድለ ቢስነት የሚያጋልጣቸው የመከራና የዋይታ አጥፊ ስልጣኔና አውዳሚ ዕውቀት እንጂ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም! ስለዚህም የስልጣኔና የዕውቀት መንገድ የመልካም ስነምግባርና የሞራላዊ እሴቶች መንገድም ጭምር ነው፡፡ ዕውቀትና ስልጣኔ የሌለበት የደስተኝነትና የመታደል መንገድ ቅዠትና ከንቱ ተረት እንደሆነ ሁሉ፣መከመልካም ስነምግባርና ከሞራላዊ እሴት የተራቆተ የዕውቀትና የስልጣኔ መንገድም ግለሰቦችን፣ማህበረሰቦችንና መላውን የሰው ልጅ ለጥፋትና ለውድመት የሚያጋልጥ መንገድ ነው፡፡

የማያነብና የማይጽፍ መልክተኛ

‹‹እነዚያ አንቀጾች ከአንድ ማንበብና መጻፍ ከማይችል ሰው እንዴት ሊመነጩ እንደሚችሉ ለማወቅ አእምሮ ግራ ይጋባል፡፡ መላው የምሥራቅ ሕዝብ በቃላቸውም ሆነ በይዘታቸው መሰሎቻቸውን የሰው ልጅ አእምሮ ማመንጨት የሚሳነው አንቀጾች መሆናቸውን አምኖ ይቀበላል፡፡››

ሄንሪ ዴ ካስትሬ

የፈረንሳይ ጦር ቀድሞ ሻምበል



የዩኒቨርስ ተአምራት

‹‹ያልተማረውና በማይማን አካባቢ ውስጥ ያደገው ሰው ሙሐመድ፣ቅዱስ ቁርኣን የገለጸቸውንና ዘመናዊው ሳይንስ እስከ ዛሬው ዘመናችን ድረስ ሊደርስባቸው የሚጥረውን የዩኒቨርስ ተአምራት እንዴት ማወቅ ቻለ?! እናም ይህ ንግግር የግድ የአላህ (ሱ.ወ.) ንግግር መሆን ይኖርበታል፡፡››

ዲዮ ሪፖርተር

በአሜሪካ የሚታተም ጋዜጣ

https://www.path-2-happiness.com/am